# ለውይይት በቀረበው ረቂቅ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የማህበራትአዋጅ ላይ በሲቭል ማኅበራት የቀረበ አማራጭ ሃሳብ

# የኢትዮጵያ ሲቭል ማኅበራት ጊዜያዊ አስተባባሪ ግብረ ኃይል

ጥቅምት ፳፻፲

አዲስ አበባ

## መግቢያ

ኢትዮጵያውያን በማህበር የመደራጀት የረጅም ጊዜ ታሪክ ቢኖረቸውም የመደረጃት መብት በተለያዩ ምክንያቶች በሚፈለገው መጠን ሊተገበር አልቻለም። በዚህም ምክንያት ለረጅም ጊዜ ለመረዳጃነት ከሚመሰረቱት ከባህላዊ ተቋማት ማለትም እንደ እድር ፤ እቁብ እና ጥቂት የሙያ ማህበራት ውጭ ሌላ ዓይነት የማህበራት አመሰራረት ሊፈጠርና ሊያድግ አልቻለም ነበር። ሆኖም በአገራችን ተከስተው የነበሩትን የድርቅ ጊዜያትን ተከትለው በዕለት ደራሽ ዕርዳታ ላይ የሚሰሩ በተለይም የውጭ አገር መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማደግ መጀመራቸውን ጥናቶች ያሣያሉ። በአገራችን ለሲቭል ማህበራት በዓይነትና በቁጥር ማደግ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ከ1983 ዓም ወዲህ የተመሰረተው አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት ለመሆኑ አጠያያቂ አይሆንም። ይህ ሥርዓት በሽግግሩ ወቅት አለም ዓቀፉን የሰብአዊ መብት መግለጫ (UDHR) ሙሉ በሙሉ ከመቀበሉም በላይ እንደ አገሪቱ ህገ መንግሥት አድርጎ በመውሰዱ(አረፍተ ነገሩ ጥያቄ ሊያስነሳ ስለሚችል እነዲሰረዝ ተጠቁመዋል) እና የተለያዩ የመደራጀት መብትን የሚያረጋግጡ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሥምምነቶችን በመቀበሉ ለሲቭል ማህበራት በዓይነትና በቁጥር ማደግ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። በተለይም ባለፉት የፖለቲካ ሥርዓቶች ውስጥ ሊታሰቡ የማይችሉት አላማቸውን ከዕለት ደራሽ እርዳታ ይልቅ በአድቮኬሲና በመብት ምስርት(Right Based) አካሄድ ላይ ያደረጉ የልማት ማህበራት ሊስፋፉና በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ጉልህ ድርሻ ሊይዙ ችለዋል። በመሆኑም ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአሁኑ ወቅት ቁጥራቸው ከ 3500 በላይ የሆኑና በፌደራል ደረጃ የተመዘገቡ ማህበራት ይገኛሉ።

የሲቭል ማህበራት አመሰራረት በኢትዮጵያ ከላይ በአጭሩ ለመግለጽ የተሞከረውን ቢመስልም እነዚህን ተቋማት ለመምራት የሚያስችሉ ህጎች መውጣት የጀመሩት ግን የአሁኑ ዓይነት ማህበራት መፈጠር ሳይጀምሩ በ1950ዎቹ አንስቶ ነው። እነዚህ ቀደምት ህግጋት ዘመናዊውን የሲቭል ማህበር ለመምራት የሚያስችል የተሟላ አቅም ሥላልነበራቸው ክፍተቱን ለመሙላት በማሰብ በአስፈፃሚ አካላት የተለያዩ ደንቦች

እንዲወጡ ግድ ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ደንቦች አሁን በሥራ ላይ ካለው ህገ መንግሥታዊ የመደራጀት መብት ዋስትና አንፃር ሲታዩ መብቱን ከማስከበር ይልቅ በመብቱ ላይ እያደረሱ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ ያመዝናል፡፡ በዚህም የተነሳ የሲቭል ማህበራት አሁን የደረሱበትን የእድገት ደረጃ እና በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 31 የተረጋገጠውን የመደራጀት መብት መሠረት ያደረገ እራሱን የቻለ ወጥ ህግ እንዲወጣ በመንግሥትና በዘርፉ አባላት ላለፉት አምስት ዓመታት የተለያዩ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ምንም እንኳን የዘርፉን አባላት ሙሉ ተቀባይነት ባያገኙም ከ1996 ዓም ጀምሮ መንግሥት የተለያዩ ረቂቅ ህጎችን በማዘጋጀት ለህዝብ ውይይት አቅርቧል፡፡

በ2000 ዓም ላይ መንግሥት የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና የማሕበራት ረቂቅ አዋጅ ለውይይት አቅርቧል፡፡[1] በዚህ ረቂቅ ህግ ላይ የሲቭል ማህበራት አባላት እንዲወያዩበትና ከመንግሥት አካላት ጋር በተለይም ከፍትህ ሚኒስትሩ እና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር እንዲወያዩበት ተደርጓል፡፡ ይህንን ሂደት በሲቭል ማህበራት በኩል ሂደቱን የሚያስተባብር ጊዚያዊ ግብረ-ኃይል ተመሥርቶ በረቂቅ ህጉ ዙሪያ ውይይቶች እንዲካሄዱና ለመንግሥት የሚቀርቡ አስተያየቶችም እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ በዚህ ግብረ-ኃይል አማካኝነት እና መንግሥትም በፈቀደው መሠረት ለውይይት በቀረበው ረቂቅ ህግ ላይ እስካሁን ድረስ ለመንግስት ሦስት አማራጭ አስተያየቶች በጽሁፍ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ከመንግሥት ጋር የተደረጉ ውይይቶች ለረቂቅ ህጉ መሻሻል እጅግ ጠቃሚ ነበሩ፡፡ ከሚያዝያ 2000 ዓም ጀምሮ ሦስት ረቂቆች የቀረቡ ሲሆን በተከታታይ የወጡት ረቂቆች የሲቭል ማህበራትን ተጠያቂነትና ነፃነት ከማረጋገጥ አኳያ መሻሻል የታየባቸው ናቸው[2]፡፡ እነዚህ አዎንታዊ ለውጦች እንደተጠበቁ ሆነው አሁንም ለውይይት የቀረበው ሦስተኛ ረቂቅ በዘመናዊና ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ሊወጣ ከሚገባው የሲቭል ማህበራት ህግ አንጻር ሲታይ ብዙ መሻሻሎችን የሚጠይቅ ሆኖ

---

[1] ይህ ለውይይት የቀረበው አዋጅ ከዚህ በፊት ቀርበው ከነበሩት ረቂቆች አንጻር ሲታይ ጥብቅ እና ቁጥጥር የበዛበት ነው፡፡

[2] ወደፊት በሥፋት እንደምናየው አሁንም ለውይይት የቀረበው ረቂቅ ህግ የሲቭል ማህበራትን ነጻነት ከማስጠበቅ አንጻር አከራካሪ የተባሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች ያለምንም ማሻሻያ እንደያዘ ነው፡፡

ተገኝቷል፡፡ እንደውም በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ወደ ኋላ የመመለስና የማጥበቅ አዝማሚያ ታይቷል፡፡[3]

የዚህ ጽሁፍ ዋንኛ አላማ መንግስት በተለይም ክቡር ጠቅለይ ሚኒስትሩ በረቂቅ ህጉ ላይ የሲቪል ማህበራት በማንኛውም ጊዜ ያላቸውን አስተያየት ማቅረብ እንደሚችሉ በገለጹት መሠረት የዘርፉ አባላት አሁንም ህጉ ከመጽደቁ በፊት ሊታዩ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ሰፊ ጊዜ ወስደው የደረሱበትን አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ያለመ ነው፡፡ የጽሁፉን ዝግጅት በሚመለከት ትኩረት ያስፈልጋቸዋል በተባሉት በእያንዳንዱ የረቂቅ ህጉ አንቀጽ ላይ ትንታኔ እና የመፍትሄ ሃሳብ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በፊት በቀረቡት አስተያየቶች መሠረት ተቀባይነት ባገኙት ጉዳዮች እና በሌሎች ክርክር ሊነሳባቸው አይችልም በተባሉት ጉዳዮች ላይ ጽሁፉ ትኩረት አላደረገም፡፡ ለትንታኔዎቹና ለመፍትሄ ሃሳቦቹ መሰረት የተደረጉት አለም ዓቀፍ ተሞክሮዎች እና ከኢትዮጵያ ጋር አንጻራዊ የእድገት ደረጃ ያላቸው አገራት ልምድ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ረቂቅ ህጉን ለመቃኘት የተሞከረው የኢፌዲሪ ህገ መንግሥትን መሠረት በማድረግ ሲሆን እንደ አስፈላጊነታቸውም ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሥምምነቶችም ከግምት ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ በጨረሻም የዘርፉ አባላት በጽሁፉ ላይ ውይይት አድርገው የሰጡት አስተያየት ተካቷል፡፡

## የጽሁፉ ዋና ዋና ግኝቶች

1. ረቂቅ ህጉ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጋጩ ድንጋጌዎችን ይዟል
    - ❖ በህገ መንግስቱ ለማንኛውም ሰው የተረጋገጠውን የመደራጀት መብት የገቢ ምንጭን መሠረት በማድረግ ለዜጎች ብቻ ይገድባል፡፡
    - ❖ በህገ መንግስቱ ለማንኛውም ህጋዊ ዓላማ መደራጀት እንደሚቻል የተመለከተውን በመጣስ የገቢ ምንጭን መሠረት በማድረግ በተወሰኑ ነገር ግን ህጋዊ በሆኑ አላማዎች ላይ መሰማራትን ይከለክላል፡፡

[3] በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ ክልክላ ያልተደረገባቸው የሥራ ዘርፎች (በሴቶች፣በሕፃናት እና በአካል ጉዳተኞች መብት ላይ የሚሰሩ ስራዎች) በሁለተኛውና ሦስተኛው ረቂቅ ላይ እንዲከለከሉ ተደርገዋል፡፡ የረቂቅ ህጉን አንቀጽ 14(5) ይመልከቱ

- ❖ አገር አቀፋዊ ሥያሜ ያለውን ድርጅት ለማቋቋም የአምስት ክልሎች ውክልና በመጠየቅ ረቂቅ ህጉ ማንኛውም ሰው በሃሳብ ከሚመሳሰሉት ሌሎች ሰዎች ጋር የመደራጀት ህገ መንግሥታዊ መብቱ እንዲገደብ ተደርጓል፡፡
- ❖ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 37 ለማንኛውም ሰው የተረጋገጠውን ፍትሕ የማግኘት መብት ረቂቅ ሕጉ የገቢ ምንጭን መሠረት በማድረግ ለኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ብቻ ይገድባል፡፡
- ❖ በሕገ መንግሥቱ ላይ ከተመለከተው በተፃራሪ ፍትሕ የማግኘት መብትን ለመሠረታዊ የህግ ስህተቶች ብቻ በማድረግ የዳኝነት ሥልጣን በሌለው የአስተዳደር መሥሪያ ቤት የተሰጠ ውሳኔን የመጨረሻ ያደርጋል፡፡
- ❖ በብዙሃን ማህበራትና በሌሎች ማህበራት መካከል ያለምንም ህጋዊ ምክንያት ልዩነት በማድረግ አድሎአዊ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል

2. ህጋዊ ሰውነት ያላቸውን ተቋማት የገቢ ምንጭን መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ወይም የውጭ በማለት በኢትዮጵያ ህግ ሥርዓት ውስጥ አዲስና ያልተለመደ ትርጉም ያስቀምጣል፡፡
3. አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የሲቭል ማህበራት ወደፊት ሊኖራቸው የሚችለው ህጋዊ አቋም የበጉ አድራጎት ማህበራት መሆኑ ቢታወቅም ህጉ ከእነዚህ አካላት ይልቅ ቁጥራቸው አነስተኛ ለሆኑት ለማህበራት ትኩረት ያደርጋል፡፡
4. ከነጻነት ይልቅ ተጠያቂነት ላይ በማተኮር የውስጥ ጉዳይ ሊሆኑ በሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ የአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ጣልቃ የሚገቡባቸውን በር ይከፍታል፡፡
5. ረቂቅ ህጉ ኢትዮጵያውያን የሲቭል ማህበራት ከውጭ ዕርዳታ ከ10% በላይ እንዳይቀበሉ ሲከለክል በአገር ውስጥ ገንዘብ ሊያገኙ የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ በተገቢው አልፈጠረም፡፡
6. ምዝገባን ለመከልከል፣ አሰራርን ለመቆጣጠር እና አንድን ድርጅት ወይም ማህበር ለማፍረስ ለኤጀንሲው የተሰጡት ሥልጣኖች ሰፊና ለትርጉም የተጋለጡ ናቸው፡፡
7. ረቂቅ ህጉ እርስ በእርስ የሚጋጩ እና ግልጽነት የጎደላቸው አንቀጾችን ይዟል፡፡

8. ከቀደምት ረቂቆች የተሻለ አንጻራዊ መሻሻል ቢኖረውም ረቂቅ ህጉ ከፍተኛ ሊባል የሚችል የወንጀል ቅጣት ይዟል፡፡
9. አዲሱን ህግ በሥራ ላይ ባሉ ድርጅቶች ላይ ያለውን ተፈጻሚነት አስመልክቶ የተቀመጠው የሽግግር ጊዜ አጭር በመሆኑ በአስፈጻሚው መሥሪያ ቤት እና በድርጅቶቹ ላይ የአፈጻጸም ችግር ማስከተሉ አይቀርም፡፡

## ዝርዝር የማሻሻያ ሐሳቦች

**<u>መቅደም /Preamble/</u>**

እንደሚታወቀው በአንድ አዋጅ ወይም ደንብ መጀመሪያ ላይ ህጉን የሚያወጣው ክፍል ህጉን ለማውጣት ያነሳሱትን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አመክንዮችን ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህንን ህግ ለማውጣት የሚያስችል ስልጣን ያገኘበትን የአገሪቱን ህገ መንግሥት ወይም ሌላ የበላይ ህግ ካለ ይህንን ያስቀምጣል፡፡ በዚህ መሠረት ረቂቅ አዋጁ ለህጉ መውጣት መነሻ የሆኑትን ጥቂት ምክንያቶች ዘርዝሯል፡፡ እነዚህም:-

1/ በኢፌዲሪ ህገ መንግሥት የተረጋገጠውን "የዜጐችን" የመደራጀት መብት ተግባራዊ ማድረግ፣
2/ የኢትዮጵያ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በኢትዮጵያ ህዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ያለባቸውን ሚና መደገፍና ማሳለጥ ናቸው፡፡

የህጉ የመጀመሪያ ዓላማ ተደርጐ የተቀመጠው በህገ መንግሥቱ የተረጋገጠውን "የዜጐችን" የመደራጀት መብት ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ከህገ መንግሥቱ አንቀጽ 31 አንፃር መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 31 እንደሚከተለው ይነበባል፡፡ "ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው፡፡ ሆኖም አግባብ ያለውን ህግ በመጣስ ወይም ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን

በህግ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ"። ህገ መንግሥቱ ላይ በግልፅ እንደሚታየው የመደራጀት መብት ለማንኛወም ሠው የተረጋገጠ መብት ነው፡ ይህ መብት በረቂቅ ህጉ ላይ እንደሚታየው ለዜጉች ብቻ የተረጋገጠ መብት አይደለም። ህገ መንግሥቱ ለኢትዮጵያውያን ወይም ለዜጎች ብቻ ተለይተው እና ለማንኛውም ሰው የተረጋገጡ ዲሞክረሲያዊ መብቶችን በግልፅ ለይቶ አስቀምጧል። በዚህም መሰረት የሚከተሉት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማንኛውም ሰው በህገ መንግሥቱ የተረረጋገጡ መብቶች ናቸው።

1. የአመለካከትና ሃሣብን በነፃ የመያዝና የመግለፅ መብት አንቀጽ 29፣
2. የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አንቀጽ 30፣
3. የመደራጀት መብት አንቀጽ 31፣
4. የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች አንቀጽ 34፣
5. የሴቶች መብት አንቀጽ 35፣
6. የህፃናት መብት አንቀጽ 36፣
7. ፍትህ የማግኘት መብት አንቀጽ 37 ናቸው።

በአንፃሩ ለኢትዮጵያውያን ወይም ለዜጎች ብቻ ተብለው በህገ መንግሥቱ ተለይተው የተቀመጡ ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. የመዘዋወር ነፃነት አንቀጽ 32፣
2. የዜግነት መብቶች አንቀጽ 33፣
3. የመምረጥና የመመረጥ መብት አንቀጽ 38፣
4. የብሔሮች ብሄረሰሶች ህዝቦች መብት አንቀጽ 39፣
5. የንብረት መብት አንቀጽ 40፣
6. የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች አንቅጽ 41፣
7. የልማት መብት አንቀጽ 43 ናቸው።

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከተው የመደራጀት እና ፍትህ የማግኘት መብት ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተከለሉ መብቶች ያለመሆናቸውንና ይልቁንም ለማንኛውም ሰው የተጠበቁ መብቶች መሆቸውን መረዳት ይቻላል። ይህ የህገ መንግሥቱ አገላለፅም ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነትቶች ጋርም በእጅጉ

የሚስማማ ነው። ይሁን እንጂ ረቂቅ ህጉ ከዚህ በተፃራሪ በመሄድ የመደራጀት መብቱን ለዜጎች ብቻ እንደተፈቀደ መብት አድርጐ ያስቀምጣል። ይህ አቀራረብ ከህገ መንግሥቱ እና ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የሚጋጭ በመሆኑ በእጅጉ እንደገና ሊጤን ይገባል።

**የማሻሻያ ሃሣብ**

*የመቅድሙ የመጀመሪያ አንቀጽ እንደሚከተለው ቢስተካከል።*

*"በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥቱ የተረጋገጠበት የሠዎችን የመደራጀት መብት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ"*

**"የኢትየጵያ"፣ "የኢትየጵያ ነዋሪዎች" እና "የውጭ" የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት** <u>**አንቀጽ 2 (2)፤(3) እና (4)**</u>

ከላይ በተጠቀሱት ንዑስ አንቀጾች ላይ እንደተመለከተው በረቂቅ ህጉ ሦስት አይነት የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት እንዳሉ መረዳት ይቻላል። እነዚህም "የኢትየጵያ"፣ "የኢትየጵያ ነዋሪዎች" እና "የውጭ" ናቸው። አይነቶች እንዲለያዩ የተደረገው በተመዘገቡት ቦታ፣ በአባላቶቻቸው ዜግነት፣ በገቢ ምንጫቸው እና አባላቱ በሚኖሩበት ቦታ መሆኑንም መገንዘብ ይቻላል።

በህግ ሥርዓት ውስጥ የኢትዮጵያን ጨምሮ ህጋዊ ሰውነት ያላቸውን ተቋማት የሀገር ውስጥና የውጭ ብሎ መመደብ የተለመደ አሠራር ሲሆን ለክፍፍሉም መሠረት የሚሆኑት ጉዳዮች እንደየአገራቱ የህግ ሥርዓት ይለያያሉ። ተቋማቱ መጀመሪያ የተመዘገቡበትና ህጋዊ ሰውነት ያገኙበትን ቦታ /አገር/፣ የተቋማቱ ዋና መስሪያ ቤት እና መደበኛ ሥራ ማከናወኛ ሥፍራን ወይም የባለቤቶቹን ዜግነት መሠረት በማድረግ ክፍፍሎች ይደረጋሉ። ይህ አይነቱ አሠራር በተለይም በንግድ ተቋማት ላይ ጐልቶ የሚታይ ነው። ይሁን እንጂ አንድ ድርጅት ሥራውን ለማከናወን የሚጠቀምበትን የገቢ ምንጭ መሠረት በማድረግ የድርጅቱን ዜግነት ለመወሰን እንደ መስፈርት የተቀመጠ አሠራር የተለመደና የታወቀ አይደለም። እንዲህ አይነት ተሞክሮ ያለውን የህግ ሥርዓት ማግኘቱ አስቸጋሪ ነው። በኢትዮጵያ የህግ ሥርዓት ውስጥም የተለመደ አሠራር አይደለም።

በረቂቅ ህጉ ላይ ስለ እነዚህ ተቋማት የተሠጡት ትርጉሞች በጥንቃቄ ሊስተዋሉና እንደገና ሊጤኑ የሚገባቸው ለመሆናቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ከላይ እንደተጠቀሰው የአንድ ድርጅት ወይም ማህበር አገራዊነት ሊታይ የሚገባው በተመዘገበበት ሥፍራ እና መደበኛ ሥራውን በሚያከናውንበት ሥፍራ መሆን አለበት እንጂ በገቢ ምንጭ መሆን የለበትም። ምክንያቱም በኤፌዲሪ ህገ መንግሥት የመደራጀት መብት ለማንኛውም ሰው ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ሆነም አልሆነም፤ የገቢ ምንጩ ከኢትዮጵያዊ ሆነም አልሆነም የተረጋገጠ ስለሆነ ዜግነትና የገቢ ምንጭ መስፈርት ሊሆኑ አይገባም። ይህንን መሠረት በማድረግም ልዩነት መፍጠር እንደ አድሎአዊ አሠራር የማይወሰድበት ምክንያት ካለመኖሩም በላይ ከህገ መንግሥቱ ጋር ይቃረናል።

በአዋጁ መግቢያ ላይ አዋጁ እንዲወጣ ካስፈለገባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የበጎ አድራጎት ድርጅት (በአድ) እና ማህበራት በኢትዮጲያ ህዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመደገፍና ለማሳለጥ መሆኑ ተመልክቷል። አዋጁ ይህንን ዓላማ ሲያስቀምጥ እነዚህ ተቋማት አሁን ካሉበት ደረጃ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንዲገኙ ለማድረግ እንጂ አሁን ካሉበት የእድገት ደረጃ እንዲያሽቆለቁሉ ለማድረግ ያለመሆኑ እሙን ነው። ኢትዮጵያዊ የሆኑ በአድ እና ማህበራት ከውጨ የሚያገኙት የገቢ መጠን ከ10% መብለጥ የለበትም ሲባል በቅድሚያ እነዚህን ተቋማት አሁን ካሉበት ደረጃ በተሻለ ሊያሠራቸው የሚችል የአገር ውስጥ የገቢ ምንጭ መኖሩን ወይም ደግሞ እንዲያገኙ የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠር የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ የግድ ይላል።

አገራችን ካለችበት አነስተኛ የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ እንዲሁም ለምግባረ ሰናይ ድርጅቶች ልገሣ የማድረግ ባህልና አቅሙ በሌለበት ሁኔታ በአድ እና ማህበራት ከአገር ውስጥ ገንዘብ በማሰባሰብ ሥራቸውን መሥራት ይችላሉ የሚለው የህጉ አቋም ወይም መንፈስ ሊጤን ይገባዋል። ሌላው ህጉ እንደዚህ አይነት ገደብ ሲያስቀምጥ ኢትዮጵያዊ በአድ እና ማህበራት በአገር ውስጥ ለሥራቸው አስፈላጊ የሆነውን የገንዘብ መጠን በአገር ውስጥ ማሰባሰብ እንዲችሉ ህጉ የፈጠረው ምቹ ሁኔታ አለ ወይ? የሚለው ነው። ወደፊት በዝርዝር እንደሚታየው ህጉ እንደነዚህ አይነት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮአል ለማለት

ያስቸግራል፡፡ እንደ ጋና በመመሳሰሉት ሌሎች አገሮች እንደሚደረገው የኢትዮጵያ በአድ እና ማህበራት የፐብሊክ ፈንድ (የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ)፣ የታክስ ቅናሽ ወይም ነፃ መሆን እድል በረቂቁ ህጉ ላይ አልተፈቀደም፡፡ በዚህ ረገድ የተፈቀደ ነገር ቢኖር በአድ እና ማህበራት በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ መሠማራት እንደሚችሉ የተቀመጠ ሲሆን ይህም በብዙ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲታጠር ተደርጓል፡፡ ሥለዚህ ያለው ነባራዊ ሁኔታው በማይፈቅድበት እና ህጉም እራሱ የተመቻቸ ሁኔታ ሣይፈጥር የኢትዮጵያዊ በጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ከውጪ የሚያገኙትን የገቢ መጠን በ10% ብቻ መወሠኑ በህጉ መግቢያ ላይ ከተቀመጠው የህጉ ዓላማ ጋር የሚሄድ አይደለም፡፡ ይህ የገንዘብ መጠን ኢትዮጵያዊ በአድ እና ማህበራት በኢትዮጵያ ህዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ውስጥ ያላቸውን ሚና ለመደገፍና ለማሳለጥ ከቶውንም የሚያስችል አይደለም፡፡

ሌላው በትርጉም ክፍሉ ውስጥ ትኩረት የሚያስፈልገው በአንቀጽ 2 (5) ላይ የተመለከተው የ "ብዙሃን ማህበራት" ትርጉም ነው፡፡ በህግ እረቂቅ ሥርዓት ውስጥ እንደሚታወቀው ለትርጉም የሚቀመጡ ጽንሰ ሃሳቦች በህጉ ውስጥ ተደጋግመው የሚመጡና የህጉ ዋነኛ አካላት ሲሆኑ ነው፡፡ በረቂቅ ህጉ ላይ የብዙን ማህበራትን በሚመለከተ የተገለፀው አንድ ቦታ ላይ ብቻ ሲሆን ከሌሎች የማህበራት አይነቶች ተለይቶ ሊታይ የሚያስችለው አላባ (Element) የለም፡፡

በአንቀጽ 2 (14) የተቀመጠው የአስተዳደራዊ ወጪ ትርጉም ክበባዊ (Circular) በመሆኑ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡ "አስተዳደራዊ ወጭ ማለት ለአስተዳደራዊ ሥራዎች አስፈላጊ የሆነ ወጪ" በሚል መቀመጡ ክበባዊ (Circular) ያደርገዋል፡፡ ይልቁንም ህጉ ከድርጅቱ ዋንኛ የዓላማ ሥራ ጋር የማይሄድ አስተዳደራዊ ሥራ ምን ማለት እንደሆነ አስቀምጦ ከዚያ በመጠቀል ለእነዚህ ሥራዎች የሚወጡ ወጪዎች አስተዳደራዊ ወጪዎች ናቸው በሚል ቢያስቀምጠው ለመረዳት ይቀላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

አንቀጽ 2(2)፡- እንደሚከተለው ቢስተካከል

አማራጭ 1

> የኢትዮጵያ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ማህበር ማለት በኢትዮጵያ ህግ መሠረት የተመሠረተ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚሰራና

ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ማለት ነው፡፡

**የአስተዳደራዊ ወጪ ትርጉም፡** የአስተዳደራዊ ወጪን ምንነት አስመልክቶ በህጉ ላይ የተሰጠው ትርጉም ክበባዊ (circular) ትርጉም በመሆኑ ሃሳቡን መረዳት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ህጉ በአንቀፅ 2(14) ላይ አስተዳደራዊ ወጪን ለመተርጎም የሞከረ ቢሆንም «አስተዳደራዊ ሥራ» የሚባሉትን ባለመተርጎሙ አንቀፁን ለመረዳት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

**አማራጭ ትርጉም**

**አንቀጽ 2(14) ቀጥተኛ የሆነ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ወጪ**

1) ቀጥተኛ ያልሆነ ወጪ ማለት ለቤት ኪራይ ለስልክ ለመብራት ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ክፍያ እና ለመሳሰሉት የሚደረግ ወጭ ማለት ነው፡፡
2) ቀጥተኛ የሆነ ወጪማለት ከላይ በቁጥር አንድ ከተጠቀሱት ውጪ ያሉ ወጪዎች ማለት ነው

<u>ቦርድ፡- አንቀጽ 7 - 10</u>

በረቂቅ ህጉ ላይ የአስተዳዳሪነት ስልጣን ከተሰጣቸው አካላት ውስጥ አንዱ ቦርዱ ነው፡፡ ይህ አካል ኤጀንሲውን ከሚያቋቁሙት ክፍሎች ውስጥ እንደ አንዱ ሆኖ በአንቀጽ 7 ላይ ተመልክቱል፡፡ ቦርዱ በመንግሥት የሚሰየሙ ሰባት አባላት የሚኖሩት ሲሆን ሁለቱ ከበአድ እና ማህበራት የሚወጣጡ ይሆናል፡፡ የቦርዱ ስልጣንና ተግባራት በአንቀጽ 9 ላይ በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን የቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓትም በአንቅጽ 10 ላይ ተቀምጧል፡፡

ከቦርዱ ጋር ተያይዞ ከሚነሱት ጥያቄዎች የመጀመሪያው የቦርዱ ተጠሪነት ነው፡፡ የቦርዱን ተጠሪነት አስመልክቶ የተቀመጠ ድንጋጌ በረቂቅ ህጉ ውስጥ የለም፡፡ በአንቀጽ 3 ላይ እንደተመለከተው ቦርዱ ኤጀንሲውን ከሚያቋቁሙት ክፍሎች እንደ አንዱ ከወሰድነው የቦርዱ ተጠሪነት የኤጀንሲው የበላይ ለሆነው ለኤጀንሲው ዳይሬክተር ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ለቦርዱ የተሰጠውን ሥልጣን ሥንመለከት ደግሞ ኤጀንሲውና የኤጀንሲው ዳይሬክተር በሚሠጡት ውሣኔ ላይ የይግባኝ ሰሚነት ሥልጣን

ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ቦርዱ የዳይሬክተሩ ተጠሪ ሆኖ እና የኤጀንሲው አንድ ክፍል ሆኖ እነዚህ አካላት የሰጡትን ውሣኔ በይግባኝ ይመለከታል የሚለው አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

በቁጥር 9 ላይ የተመለከቱትን የቦርዱን ስልጣን በማየት ይህ ቦርድ የኤጀንሲው የበላይ አካል እንደሆነ አድርጐም መገመት ይቻል ይሆናል፡፡ ነገር ግን የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በቁጥር 11 ላይ እንደተመለከተው ተጠሪነቱ ለፍትህ ሚኒስትሩ ነው፡፡ ዳይሬክተሩ ሥራውን የሚሠራው ከሚኒስትሩ በሚሠጠው አጠቃላይ መመሪያ መሆኑ በቁጥር 11 ላይ ተመልክቶአል፡፡ በአንፃሩ በቁጥር 9 ላይ ከአዋጁ ጋር ተያይዘው የሚነሱ የፖሊሲ ጉዳዮችን፣ የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አሥተዳደርን በተመለከተ ለሚያጋጥሙ ችግሮች፣ የኤጀንሲው ዳይሬክተር በሚሠጠው ውሣኔ ላይ፣ በኤጀንሲው የሚወጡ መመሪያዎችን እና ሌሎች ጉዳዮችን ቦርዱ የመወሰን ስልጣን እንዳለው ተመልክቷል፡፡ ይህ ደግሞ በተጨማሪ የቦርዱን ብቻ ሣይሆን የኤጀንሲውን ዳይሬክተር ተጠሪነትም አሻሚ አድርጎታል፡፡ ለምሳሌ በረቂቅ ህጉ ውስጥ ከተመለከቱት አንቀጾች ውስጥ አንቀጽ 105 (2)ን ብናይ ቦርዱ ከኤጀንሲው የተለየ አቋም ያለው ያስመስላል፡፡ «በማናቸውም ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል» ይላል፡፡ ቦርዱና ኤጀንሲው የተለያየ አቋም የላቸውም የሚባል ከሆነ በረቂቅ ህጉ ውስጥ የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አስተዳደርን በሚመለከት የተሰጡ ስልጣኖች መወሰን ያለባቸው በኤጀንሲው ሣይሆን በዳይሬክተሩ መሆን ነበረበት፡፡ እንደዚህ ሆኖ ከተቀመጠ በቦርዱና በዳይሬክተሩ መካከል እንዳለ የሥራ ክፍፍል አድርጐ መረዳት ይቻላል፡፡

ሌላው ነጥብ የቦርድ አባላት የሚሰየሙት በመንግሥት እንደሆነ በአንቀጽ 9 ላይ የተመለከተው ነው፡፡ የትኛው የመንግሥት አካል ይህ ሥልጣን እንዳለው ህጉ የሚለው ነገር የለም፡፡ ከዚህ ጋር ተያያዞ ሌላ የሚነሳው ጥያቄ የቦርድ አባላት ተጠሪነታቸው ለዚህ ለመረጣቸው አካል ይሆን ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በአንቀጽ 7 ላይ ቦርዱ የኤጀንሲው አንድ አካል ተደርጎ ከተቀመጠው ጋር አይሄድም፡፡

ከቦርዱ ጋር ተያይዞ ሌላው የሚነሣው ጥያቄ በቦርዱ ውስጥ ያሉት የበጐ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ተወካይ ቁጥር ማነሱ ነው፡፡ ይህ ቦርድ የበጐ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ጥቅምና ፍላጐት እንዲሁም ተጠያቂነትና ነፃነታቸውን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ያለው እንዲሆን የተወካዮች ቁጥር ከፍ ሊል ይገባል፡፡ የተወካዮቹን አመራረጥ በሚመለከት መስፈርቱ

እና የአመራረጥ ሥርዓቱ በህጉ ውስጥ ቢገለጽ ወይም ይህን አስመልክቶ ደንብ እንደሚወጣ እንኳን ቢደረገ በቂ ነው፡፡ የቦርዱን ስብጥር በሚመለከት ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተለይም ከተጠቃሚው ህብረተሰብ ቢጨመርበት የቦርዱን ሥራ ይበልጥ ውጤታማ ማድረግ ያስችላል፡፡(ይህ ዓረፍተ ነገር የሚሰረዝ ይሆናል)

ማሻሻያ ሀሳብ፡

1. በቦርዱ ውስጥ ያሉት የበአድ እና ማህበራት ተወካይ ቁጥር ወደ ሶስት ቢያድግ
2. የቦርዱ ሰብሳቢ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንት እነዲሆኑ ቢደረግ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ባህሪ ካላቸው ተቀማት ቢሆን፡፡
3. በቦርዱ ውስጥ ያሉት የበአድ እና ማህበራት ተወካዮች በራሳቸው በበአድ እና ማህበራት የሚመረጡ እነደሆነ በአዋጁ ውስጥ ቢካተት ( ይህ በቀይ የደመቀው የማሻሻያ ሀሳብ የተጨመረ ነው፡፡)

**አንቀጽ 14**

ይህ አንቀጽ የበጐ አድራጐት ድርጅት ትርጉም፤ ዓላማ እና የበጐ አድራጐት ሥራ ምን ምን ሊያጠቃልል እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ የበጐ አድራጐት ሥራ ህዝባዊ ጥቅም አለው ተብሎ የሚገመተው ምን ምን ነገሮችን ሲሟሉ እንደሆነም ያብራራል፡፡ ሌላው በአንቀጹ ውስጥ ተካቶ የምናገኘው ለኢትዮጵያዊያን በጐ አድራጐት ድርጅቶች ተለይተው የተከለሉ የሥራ ዝርዝሮች ወይም ዓላማዎችን ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ ላይ በዋነኛነት ትኩረትን ስቦ የምናገኘው በአንቀጹ ተራ ቁጥር 5 ላይ የተመለከተውንና ለኢትዮስያውያን በጐ አድራጐት ድርጅቶች ብቻ የተከለለውን የሥራ መስክ ወይም የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ዓላማ ነው፡፡ በአንቀጹ በተራ ቁጥረ 2 ላይ ከተዘረዘሩት የበጐ አድራጐት ዓላማዎች ውስጥ ፡-

- በሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች፣
- የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ የጾታና የሃይማናት እኩልነት መረጋገጥ በማበረታታት፣
- የህፃናትና የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበርን በማበረታታት፣
- የግጭት አፈታት ወይም እርቅን በማስፋፋት፣

- የፍትህና የህግ ማስፈፀም አገልግሎቶችን ቀልጣፋነት በማጠናከር ሥራ ላይ ከኢትዮጵያውያን በጐ አድራጐት ድርጅቶች በቀር ሌሎቹ ማለትም የኢትዮጳያውያን ነዋሪዎች እና የውጭ በአድ ሊሠማሩ አይችሉም፡፡

በአድ ወይም ማህበራት በመደራጀት መብት ውስጥ ከተረጋገጡላቸው መብቶች አንዱና ዋንኛው ህጋዊ በሆነ በማንኛውም በመረጡት የሥራ መስክ የመሠማራት መብት ነው፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 31 በግልጽ እንዳስቀመጠው ማንኛውም ሰው (የዜግነት ወይም የመኖሪያ ሥፍራ ልዩነት ሣይኖርበት) ለማንኛውም ህጋዊ ዓላማ የመደራጀት መብት እንዳለው በማያሻማ ሁኔታ ደንግጓል፡፡ በመሆኑም የረቂቅ ህጉ አንቀጽ 14 (5) ሊታይ የሚገባው ከዚህ ህገ መንግሥታዊ ዋስትና አንፃር መሆን አለበት፡፡ አሁን እንደተቀመጠው የረቂቅ ህጉ በኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ባልሆኑ ሠዎች መካከል ልዩነት ያደርጋል፡፡ ይህ ልዩነት ግን በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 31 እና የሃገሪቱ የህግ አካል በሆኑት አለም አቀፍ ሥምምነቶች መሠረት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በመደራጀት መብት ላይ የሚጣል ገደብ ምን ሊመስል እንደሚገባው በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 31 እና ኢትዮጵያ በፈረመችው አለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 22 ላይ ተቀምጧል፡፡ የሚጣለው ገደብ ግልፅና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ማህበረሰብ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ ህጋዊ የሆነ ዓላማን ለማሣካት መሆን አለበት፡፡ ኢትዮጵያውያን ነዋሪዎች እና የውጭ በአድ ከላይ በተጠቀሱት የመደራጀት ዓላማዎች ውስጥ ቢሣተፉ አገራችን ግልፅና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ማህበረሰብ ለመፍጠር በምታደርገው ጥረት ውስጥ የሚያስከትሉት ጉዳት ምን እንደሚሆን ለማወቅ አዳጋች ነው፡፡

ከሁሉም በላይ ደገሞ የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች የተገፉና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሆኑ የራሣቸውን መብት በራሣቸው ገንዘብ ለማስከበር እጅግ ከባድ የሚሆንባቸው ወይም ፈጽሞ ማስከበር የማይችሉ ሴቶች፤ ህጻናትና አካል ጉዳተኞች ከውጭ በሚገኝ የገንዘብ እርዳታ መብታቸው እንዲከበርላቸው መጠየቃቸው ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው አዎንታዊ አስተዋፅኦ ከማድረግ በቀር የሚያመጣው ችግር አይኖርም፡፡ በአድ እና

ማህበራት እስካሁን ባላቸው ተሞክሮ በሃገሪቱ ውስጥ በሚካሄደው የመልካም አስተዳደር ሥርዓት ማስፈን እና የፍትህ አካላትን አቅም በመገንባትና ቀልጣፋ እንዲሆኑ በማድረግ ጥረት ውስጥ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ይታወቃል፡፡ በዚህም ጥረታቸው መንግሥት ግልፅና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ማህበረሰብ ለመፍጠር እያደረገ ላለው ጥረት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ይህ ሁሉ አስተዋጽኦ የተደረገው ግን ከውጪ በአገኙት ገንዘብ መሆኑ አይካድም፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በአንቀጽ 14 ንዑስ ቁጥር 5 ላይ የተቀመጠው ገደብ ቢነሳ

የበጎ አድራጎት ማህበራትና የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች አንቀጽ 47

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የበጎ አድራጎት ማህበር ማለት ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተቋቋመ ማህበር ነው፡፡ በአንቀጽ 48 መሠረት ደግሞ አግባብነት ያላቸው ማህበራትን እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን የሚመለከቱ የአዋጁ ድንጋጌዎች ለበጎ አድራጎት ማህበር ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

አሁን ባለው የሲቪል ማህበራት አደረጃጀት ተጨባጭ ሁኔታ  ብዛት ያላቸው አገር በቀል ድርጅቶች ወደ የበጎ አድራጎት ማህበርነት ይቀየራሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ በረቂቅ ህጉ ውስጥ እነዚህ ማህበራት ጠንካራ ድጋፍ የሚሰጧቸው ዝርዝር አንቀጾች ሊኖሩዋቸው ይገባል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ንዑስ አንቀጾች ያለምንም ለውጥ በሁለተኛው ረቂቅ ውስጥ ስለገቡ የማሻሻያ ሀሳቡ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ቀደም ሲል በቀረበው ሀሳብ መሠረት የበጎ አድራጎት ማህበራት ሊኖራቸው ከሚችለው ማህበራዊ ጠቀሜታ አንጻር ዝርዝርና የተለየ የሕግ ማእቀፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ለማህበራት የተደነገጉ አንቀጾችን በእነርሱ ላይ ተፈጻሚ ማድረግ የበለጠ ችግር ይፈጥር እንደሆን እንጂ መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ አቋማቸው በግልጽ ሊደነገግ ይገባል፡፡ እንደ ማህበራት ቢቆጠሩ የተሻለ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡

አንቀጽ 49-55 የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎች

በአንቀጽ 53(3) በተደነገገው መሠረት በኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ የታሰበውን ዓላማ ለማሳካት በቂ ካልሆነ ገንዘቡ ለሌላ ሥራ እንደሚውልና ገንዘቡን ወይም ንብረቱን የሰጡ

ሰዎች መልሰው ሊወስዱት እንደማይችሉ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ለጋሾች ገንዘባቸውን ወይም ንብረታቸውን የማስመለስ መብት ለምን እንደተነፈጋቸው ግልጽ አይደለም፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ከለጋሾች አንጻር በልግስና የተሰጠ ገንዘብ ወይም ንብረት ለታለመለት ዓላማ መዋል ይኖርበታል፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ ስጦታውን የማስመለስ ወይም ለሌላ የበጎ አድራጎት አላማ መስጠት በለጋሹ የሚወስነው ጉዳይ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም ንዑስ አንቀጹ ለጋሾች ስጦታቸውን የማስመለስ መብት ሊኖራቸው በሚገባ መንገድ መሻሻል ይኖርበታል፡፡

<u>ማህበራት፡- አንቀጽ 56</u>

<u>ትርጓሜ፡-</u> በአንቀጽ 56(1) መሠረት ማህበር ማለት ዓላማው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ ማናቸውም ሕጋዊ አላማዎች ያሉት የሰዎች ስብስብ ነው፡፡ ትርጉሙ በሰፊ መንገድ በመደንገጉ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ማህበራትን ለማካተት ጠቃሚ ነው፡፡ በተጨማሪም በቀድሞው ረቂቅ መሠረት አንድን ማህበር ለማቋቋም ቢያንስ አስር ወይም አምስት ሰዎች ሊኖሩ እንደሚገባው ተደንግጎ የነበረው ቀሪ መደረጉ የሚያስመሰግን ነው፡፡ ስለዚህም ንዑስ አንቀጹ አሁን ባለበት ሁኔታ ተጨማሪ የማሻሻያ ሀሳብ የሚቀርብበት አይሆንም፡፡

በአንቀጽ 56(2) ድንጋጌ መሠረት ማህበራት ስራዎቻቸውን የሚያስተባብር የማህበራት ህብረት ማቋቋም ይችላሉ፡፡ ይህ መብት አሁን በሥራ ላይ ባሉት ህጎች የተከለከለ ባይሆንም በግልጽ ሕጋዊ እውቅና ማግኘቱ የሚያስመሰግን ነው፡፡ ሆኖም ህብረቱ ስራዎችን ለማስተባበር ብቻ ሳይሆን ህጋዊ ሰውነት ኖሮት የጋራ ጥቅሞችን ለማራመድና ለመከላከልም ጭምር መሆኑ መመልከት አለበት፡፡

<u>የማሻሻያ ሐሳብ</u>

በማህበራቱ ህብረት ዓላማ ላይ የተጣለው ገደብ አላስፈላጊ በመሆኑ ይኸው ተሰርዞ መብቱ ያለ ገደብ ሊደነገግ ይገባዋል፡፡ እንዲሁም ህብረቱ ህጋዊ ሰውነት ሊኖረው በሚችል መልኩ ሊቋቋም እንደሚችል በግልጽ መደንገግ አለበት፡፡

<u>የማህበራት መብቶችና ግዴታዎች፡- አንቀጽ 58</u>

ይህ ድንጋጌ የአባላትን መብቶችና ግዴታዎች፤የክልል ውክልና እና ኢትዮጵያውያን ብዙሃን ማህበራት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በምርጫ ሂደት ያላቸውን የመሳተፍ መብት ያስቀምጣል፡፡ የሲቭል ማህበረሰቡ በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ ይህን

ድንጋጌ አስመልክቶ ያቀረበው የማሻሻያ ሃሳብ በሁለተኛው ረቂቅ ላይ ከግምት ውስጥ አልገባም፡፡ ሥለዚህ ቀደም ሲል ቀርበው የነበሩት ተቃውሞዎቹና የማሻሻያ ሀሳቦቹ አሁንም ሊጤኑና ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

አዲስ አባላትን መቀበል፡- በንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት አንድ ማህበር የማህበሩን መስፈርት ለሚያሟላ አዲስ አባል ክፍት መሆን ያለበት ሲሆን በንኡስ አንቀጽ 4 መሠረት ደግሞ ማናቸውም ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ካልሆነ በቀር አባላትን ሊቀበልና ሊያሰናብት አይችልም፡፡ እነዚህ ሁለት ንዑስ አንቀጾች እርስ በእርስ የሚቃረኑ ይመስላሉ፡፡ በሁለቱ መካከል ግጭት ቢፈጠር የትኛው ይበልጥ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው ግልጽ አይደለም፡፡ አንድ ማህበር የአባልነት መመዘኛዎችንና የአባላትን መጠን በደንቡ ከወሰነ ክፍት ቦታ ከሌለ በቀር መመዘኛዎችን የሚያሟላ አዲስ አባል ሊቀበል አይገደድም፡፡ የአንቀጹ መንፈስ ክፍት የአባልነት ቦታ ባይኖርም መመዘኛዎቹን የሚያሟላ ሁሉ በአባልነት መግባት ይችላሉ የሚል ከሆነ ግን በማህበራት ላይ አላስፈላጊ ችግር የሚፈጥር ይሆናል፡፡ ስለዚህም በንዑስ ቁጥር 1 ላይ የተመለከተው ግዴታ ሊነሳ ይገባዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አንቀጹ ብዙ አባላት ያሏቸውን ማህበራትን እንጂ ጥቂት አባላት ያሏቸውን በቦርድ ሊመሩ የሚችሉ የበጎ አድራጎት ማህበራትን ግምት ውስጥ ያስገባ አይመስልም፡፡ በመሆኑም አንቀጹ እነዚህን ችግሮች በሚፈታ መልኩ መሻሻል ይኖርበታል፡፡

**የክልል አባላት ውክልና፡-** የፌዴራል ባህሪ እና ስያሜ ያላቸው ማህበራት የሥራ ቦታዎቻቸውና የአባሎቻቸው ጥንቅር ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ደንግጓል፡፡ ይህ ገደብ በማህበራት መብት ላይ ጣልቃ ገብነትን የሚጋብዝ ነው በማለት ተቃውሞ እና የማሻሻያ ሀሳብ የቀረበበት ቢሆንም ተቀባይነትን ሳያገኝ በሁለተኛው ረቂቅ ላይ እንዳለ ተቀምጧል፡፡ ይህ ገደብ በሕገ መንግስቱ በተደነገጉት የመብት ገደቦች የማይታቀፍ በመሆኑ በረቂቁ ውስጥ የተቀመጠበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ አንድ ማህበር በየትኛውም ክልል መስራት እንዳለበት መወሰን የውስጥ ጉዳዩ እንጂ የሕጉን ጣልቃ ገብነት የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአባላት ጥንቅርም መወሰን ያለበት በዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 4 እንደተመለከተው በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት መሆን አለበት፡፡

**ኢትዮጵያውያን ብዙሀን ማህበራት፡-** በንኡስ አንቀጽ 5 መሠረት ኢትዮጵያውያን ብዙሀን ማህበራት በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና በምርጫ ሂደት በተለይም ትምህርታዊ

ሴሚናሮችን በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በማዘጋጀት የተወዳዳሪዎችን ፕሮግራም በመረዳት የምርጫ ሂደቶችን በመታዘብና ከምርጫ አስፈጻሚዎች ጋር በመተባበር ረገድ በንቃት መሳተፍ እንደሚችሉ ተመልክቷል፡፡ በአንቀጽ 2 (12) መሠረት ብዙሀን ማህበራት ማለት የሙያ ማህበራትን፣ የሴቶች ማህበራትን፣ የወጣት ማህበራትንና ሌሎች ተመሳሳይ የኢትዮጵያ ማህበራትን ያካትታል፡፡ የሁለቱ ንዑስ አንቀጾች የተለያዩ ትርጉሞችን የሚጋብዙ ናቸው፡፡ በዚሁም መሠረት አንደኛ ለብዙሀን ማህበራት የተሰጠው ትርጉም ዝግ ሳይሆን ክፍት ነው፡፡ ማለትም ሌሎች ተመሳሳይ ማህበራት ተካትተዋል፡፡ ሁለተኛ በንኡስ አንቀጽ 5 በተዘረዘሩት መስኮች መሰማራት ግዴታ ሳይሆን ውዴታ ነው፡፡

ሶስተኛ በዚሁ ንኡስ አንቀጽ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ሊሳተፉ አይችሉም ተብሎ በግልጽ አልተደነገገም፡፡ አራተኛ ይህ ድንጋጌ የምርጫ ቦርድን ሥልጣን ለመወሰን በ1999 ዓም ተሻሽሎ ከወጣው አዋጅ ጋር ይጋጫል፡፡ ምን ዓይነት ማህበራት በምርጫ እና በሥነ ዜጋ ትምህርት ላይ መሳተፍ እንደሚችሉ የመወሰን ሥልጣን የቦርዱ እንደሆነ በዚህ በተሻሻለው የምርጫ ህግ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት መብቶቹን ለብዙሀን ማህበራ ብቻ መስጠት ያስፈለገበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በየግላቸው በተሰማሩባቸው ሕጋዊ የሥራ መስኮች የመሰማራት መብት ስላላቸው ለብዙሀን ማህበራት የተሰጡት መብቶች አድሎአዊ አሰራርን ሥለሚፈጥር አላስፈላጊ ናቸው፡፡ በመሆኑም ሊሰረዙ ይገባል፡፡ ከንዑስ አንቀጹ በስተጀርባ ያለው ሀሳብ ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በእነዚህ ዘርፎች ሊሳተፉ አይችሉም የሚል ከሆነ ግን ሕገ መንግስቱ ይህን ገደብ ባለማስቀመጡ ድንጋጌው ኢ-ሕገመንግስታዊ ገደብ ይሆናል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳቦች፡-</u>

- አዲስ አባላትን መቀበልን በተመለከተ ጉዳዩን ለማህበራቱ የውስጥ አሰራር በመተው እና ገደቡ ከተወሰነ ቁጥር በላይ አባላት ያሏቸውን ማህበራት ብቻ ይመለከታል ብሎ በመደንገግ ችግሩ ሊፈታ ይገባዋል፡፡
- የአምስት ክልሎች ውክልናን በተመለከተ የተቀመጠው ገደብ ጠቀሜታ የሌለው እና የሰዎችን ከፈለጉት ሰው ጋር የመደራጀት መብትን የሚጎዳ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባዋል፡፡
- የዲሞክራሲያዊ ግንባታንና ምርጫን በተመለከተ ለብዙሀን ማህበራት የተሰጡት መብቶች ሊሰረዙ ይገባል፡፡ ከምርጫ ህጉ አንጻርም ሊጣኑ ይገባል፡፡

**የማህበራት አደረጃጀት:- አንቀጽ 59**

በዚህ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር (1) እና (2) መሠረት የማናቸውም ማህበራት አደረጃጀት በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ቢሆንም ማናቸው ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ኦዲተር የያዘ መሆን አለበት:: እነዚህ ንዑስ አንቀጾች በቅድሚያ ግልጽነት ይጎድላቸዋል:: አንደኛ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማለት ምን እንደሆነ ትርጉም አልተሰጠውም:: ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያስፈልገው ብዙ አባላት ላሏቸው ወይም በቦርድ ለሚተዳደሩት የበጎ አድራጎት ማህበራትም ጭምር መሆኑ በግልጽ አልተደነገገም:: ሦስተኛ የማህበሩ አደረጃጀት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን እንደሚጨምር የተገለጸ ቢሆንም ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎችም ይሁን ሌላ ቦታ ላይ የዚህ ኮሚቴ ሥልጣንና ኃላፊነት እንደሌሎቹ አካላት አልተመለከተም:: አራተኛ በሥራ አስፈጻሚና በሥራ መሪ መካከል ያለው ልዩነት ወይም አንድነት ምንድነው የሚለውም በግልጽ አይታወቅም::

<u>የማሻሻያ ሀሳብ:-</u> የሥራ አስፈጻሚ ለሚለው ሐረግ ትርጉም ቢሰጥ ነገር ግን ሥልጣንና ኃላፊነቱ በማህበሩ ደንብ ሊወሰን እንደሚችል ቢመለከት ማህበራት መዋቅሮቻቸውን ተስማሚ በሆነ መንገድ እንዲያዋቅሩ ያስችላቸዋል:: ጠቅላላ ጉባኤን በተመለከተ በአዛዥነት የተደነገገው ይህ ግዴታው ብዙ አባላት ያሏቸውን ማህበራት ብቻ የሚመለከት መሆኑና በቦርድ (ሥራ አስፈጻሚ) የሚመሩ ማህበራት ግን የመስራቾቹ ወይም የባለ ድርሻዎች ስብሰባ በቂ መሆኑን በማመልከት ረቂቁ ሊሻሻል ይገባዋል::

**ከጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች መለየት:- አንቀጽ 61**

አንቀጹ የተለየ ሀሳብ ያለው አባል የልዩነት ሀሳቡን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ የማስፈር መብት እንዳለውና በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሳኔ የአገሪቱን ሕግ፣ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችን ይጥሳል ብሎ ሲያምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት እንደሚችል ደንግጓል:: ከዚህ ድንጋጌ ጋር በተያያዘ አንድ የማህበር አባል የልዩነት ሀሳቡን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ የማስፈር መብት እንዳለው መቀመጡ ተገቢ ሲሆን ማንኛውም አባል የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ህግን ወይም መተዳደሪያ ደንቡን የሚጥስ ሆኖ ከታየው ለኤጀንሲው ማመልከት እንደሚችል መቀመጡ በአባላት መካከል ቅራኔን ከሚጋብዝ እና በኤጀንሲው ላይም የሥራ ጫና ከሚፈጥር በቀር የሚሰጠው የጎላ አስተዋጽኦ የለም:: በአባላት መካከል አለመግባባት ካለ እንዲሁም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም ህግ ከተጣሰ ይህ ድንጋጌ ኖረም አልኖረም ከማመልከት የሚከለክላቸው ነገር የለም:: ከዚህ በተጨማሪ በጠቅላላ ጉባኤው

የተላለፈው ውሳኔ ለኤጀንሲው ሥለሚላክ ኤጀንሲው የውሳኔውን ህጋዊነት በቀላሉ ሌላ አመልካች ሳያስፈልገው ማወቅ ይችላል።

**የማሻሻያ ሃሳብ**

ማንናውም አባል የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ህግን ወይም መተዳደሪያ ደንቡን የሚጥስ ሆኖ ከታየው ለኤጀንሲው ማመልከት እንደሚችል የተጠቀሰው ከአንቀጹ ቢወጣ።

**የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች:- አንቀጽ 62**

አንቀጹ ከደነገጋቸው መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ። ሊቀ መንበሩ በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ ከሆነ ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሊቀ መንበሩ አማካይነት ወይም በራሱ ተነሳሽነት የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣ የማህበሩ ምልዐተ ጉባኤ በመሠረቱ በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን ቢሆንም ደንቡ ከማህበሩ አባላት ከሀምሳ በመቶ በታች ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይኖራል ብሎ መደንገግ አይችልም፣ ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ምልዐተ ጉባኤ ካልተሟላ በሚቀጥለው ሶስተኛ ስብሰባ ከአባላቱ 50% ባይገኙም በኤጀንሲው ውሳኔ ምልዐተ ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጠራል።

እነዚህ ንዑስ አንቀጾች ጣልቃ ገብነትን የሚጋብዙ ናቸው። በህጉ በተጠቀሰው 30 ቀናት ውስጥ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይጠራ ይችላል። ይህ ምክንያት ሳይጣራ ቀን ሥላለፈና አንድ አባል ሥለጠየቀ ብቻ ጉባኤው በአስገዳጅነት እንዲጠራ ከዚህም አልፎ ኤጀንሲው ሊቀመንበር እንዲሰይም መደረጉ ጣልቃ ገብነት ነው።

በማህበራትም ሆነ በንግድ ድርጅቶች የተለመደ አሰራር ጠቅላላ ጉባኤውን መጥራት በመተዳደሪያ ደንቦች የሚመራ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ ጣልቃ መግባት አስፈላጊ የሚሆነው ስብሰባው ባይጠራ የአባላት መብት በእጅጉ የሚጎዳ ሲሆን እንጂ በሁሉም ሁኔታዎች አይደለም። ስለዚህም ሕጉ ይህን ጉዳይ ለማህበራቱ ቢተውና ጣልቃ ገብነት አግባብነት የሚኖረው ከአባላት ብዙዎቹ ሲጠይቁና ለከባድ ጉዳዮች ብቻ ሊሆን ይገባል።

<u>የማሻሻያ ሀሳቦች:-</u>

- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሰብሳቢው በቂ ባልሆነ ምክንያት በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ ከሆነና ለመጥራትም

ፍቃደኛ ካልሆነ 1/3ኛ የሚሆኑት መደበኛ አባለት ለኤጀንሲው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ሥብሰባውን እንዲጠራ ወይም ያልጠራበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ኤጀንሲው የማህበሩን ሰብሳቢ ሊጠይቀው ይችላል::

- ኤጀንሲው ሥብሰባው ያልተጠራበትን ምክንያት መርምሮ ሥብሰባውን ላለመጥራት በሰብሳቢው የቀረበው ምክንያት በቂ ሆኖ ካላገኘው በ30 ቀናት ውስጥ ሥብሰባውን እንዲጠራ ሊያዘው ይችላል፡፡
- ሰብሳቢው በኤጀንሲው በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ሥብሰባውን ባይጠራ በኤጀንሲው አማካይነት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
- የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት ከሆነ የዕለቱን ስብሰባ ለመምራት ሊቀመንበር የሚሆን ሰው አባላቱ እንዲመርጡ_ኤጀንሲው ያደርጋል፡፡
- የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ስብሰባ ለመጥራት ሁሉም ሊያውቀው የሚችል ማስታወቂያ ማውጣት አለበት፡፡
- የማህበሩ ምልዐተ ጉባኤ <u>የውክልና ተሳትፎን ሥርዓት ጨምሮ</u> በመተዳደሪያ ደንቡ በተወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡ ይህን የሚመለከት ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ የስብሰባው አብዛኛው አባላት ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይኖራል፡፡ ሆኖም መተዳደሪያ ደንቡ ከማህበሩ አባላት ከ50% በታች ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይኖራል ብሎ መደንገግ አይችልም፡፡ ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች <u>ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በሚቀጥለው ሦስተኛ ስብሰባ ከአባላቱ 50% ባይገኙም ምልዓት ጉባዔ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡</u>

**የኦዲተር ሥልጣንና ተግባር:- አንቀጽ 63**

በማህበራት አደረጃጀት ኦዲተር አንድ የአሰተዳደር ክፍል ሆኖ በረቂቅ ህጉ ላይ ተመልክቷል፡፡ የኦዲተሩን ሥልጣንና ተግባር በሚመለከት በአንቀጽ 63 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ አካል የማህበሩን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፤ የድርጅቱን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በማዘጋጀት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡ ይህ አንቀጽ የውስጥና የውጭ ኦዲተሮችን ባለመለየቱ ቅሬታ የቀረበበት ሲሆን ጉዳዩ የውጭ ኦዲተርን ብቻ

የሚመለከት መሆኑን በሚያሳይ መንገድ ሊደነገግ እንደሚገባ በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ ሀሳብ ቀርቦበት ነበር:: ሆኖም የማሻሻያ ሀሳቡ ተቀባይነትን ያገኘ አይመስልም:: የኦዲተሩ ሥልጣን የውስጥ ኦዲት ከማዘጋጀት አንጻር ተደርጎ መቀመጡን ሥናይ አንቀጹ የሚያወራው ሥለውስጥ ኦዲተር ይመስላል:: ነገር ግን ኦዲተሩ የሚቀጠረው በሥራ አስፈጻሚ (ቦርድ ወይም ሥራ መሪ) ሳይሆን በጠቅላላ ጉባኤ መሆኑን ሥንመለከት አንቀጹ የሚያወራው ሥለውጭ ኦዲተር ይመስላል::

የውስጥ ኦዲተር የድርጅቱን የዕለት ከዕለት የሂሳብ እንቅስቃሴ የሚከታተል ግለሰብ ባለሙያ ሲሆን የውጭ ኦዲተር ግን በድርጅትነት የተቋቋመ አካል ሊሆን ይችላል:: በግለሰብ ደረጃ ያለን ባለሙያ የሥራ ቅጥር የጠቅላላ ጉበኤ እንዲያካሂድ መደረጉ ለአፈጻጸም ከማስቸገሩም በላይ የግለሰቡን የሥራ ብቃትና ተጠሪነትም መቆጣጠር እጅግ አስቸጋሪ ያደርገዋል:: ይህ ኦዲተር ሥራ ባቋረጠ ቁጥር ጠቅላላ ጉባኤ እየተሰበሰበ ኦዲተር ሊቀጥር ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ከውስጥ ኦዲተሩ የበለጠ የስራ ኃላፊነት ያለበትን «የስራ መሪውን» እንኳን ለመምረጥ ሥልጣን ያልተሰጠው ጠቅላላ ጉባኤ ለምን ኦዲተሩን ብቻ እንዲሰይም እንዳስፈለገ የሚታወቅ ነገር የለም::

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፡-</u>

አንቀጽ 63 እንደሚከተለው ቢስተካከል::

<u>የውጭ ኦዲተር ሥልጣንና ተግባራት</u>

ኦዲተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር አለው፤

1. የማህበሩን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል
2. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት የድርጅቱን ኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል::
3. በዚህ አዋጅ ስለ ውጭ ኦዲት የተደነገጉት ቢኖሩም ማሕበሩ በማንኛውም ጊዜ በውስጥ ኦዲተር ሊጠቀም ይችላል::

<u>አባላትን የሚመለከቱ መረጃዎች፡-</u> አንቀጽ 64

አንቀጹ ከደነገጋቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ይገኙበታል:: የማህበሩ የሥራ መሪዎች የአባላቱን ዝርዝር ጉዳዮች ይመዘግባሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ሲጠየቁ ለኤጀንሲው ያቀርባሉ:: ከማህበራት የሚፈለጉ መረጃዎች ዝርዝር ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ እንደሚወሰን አንቀጹ ያስቀምጣል:: ከዚህ አንቀጽ ጋር ተያይዞ የሚነሳው አሳሳቢ ጉዳይ አባላትን አስመልክቶ የሚፈለገው ዝርዝር መረጃ በህገ መንግሥቱ ላይ የግል ህይወት

ምስጢርን የመጠበቅ መብት ጋር ነው:: ይህ አንቀጽ በጥንቃቄ ካልተያዘ በህገ መንግስቱ ላይ የተጠበቀውን የግለሰቦችን የግል ህይወት ምስጢርን ሊጎዳ ይችላል:: በመሆኑም ተፈላጊው ዝርዝር ከተለመደው ማንነትን የመግለጽ ጉዳይ በላይ ሊሆን አይገባም:: ተፈላጊውን ዝርዝርም በደንብ ከመወሰን ይልቅ አዋጁ ላይ ሊመለከት ይገባዋል::

<u>የማሻሻያ ሀሳቦች:-</u> የአባላት መረጃ ዝርዝሮች የሲቪል ማህበረሰቡ ሊቆጣጠራቸው በማይችሉ መመሪያዎች ከመደንገጋቸው ይልቅ በዚህ ሕግ ቢደነገጉ ተመራጭ ይሆናል:: በተጨማሪም ዝርዝሮቹ በተቻለ መጠን ጠቅላላ ሆነው የአባላትን የግል ጉዳዮች የማይመለከቱ መሆን ይኖርባቸዋል:: እንዲህ አይነት አጠቃላይ ዝርዝሮች አባልነትን ያበረታታሉ ተብሎ ይታመናል:: በመሆኑም አንቀጹ እንደሚከተለው ቢስተካከል::

1. የማሕበሩ የሥራ መሪዎች የአባላቱን ማንነትና አድራሻ ይመዘግባሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ሲጠየቁ ለኤጀንሲው ያቀርባሉ::
2. ቢሰረዝ

### የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አመሰራረት ፍቃድ አሰጣጥና ምዝገባ

**አመሰራረት:-አንቀጽ 65 እና 66**

በአንቀጽ 65 ድንጋጌዎች መሠረት ማናቸውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በተመሰረተ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ለምዝገባ ማመልከት አለበት:: ሆኖም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በቂ ምክንያት መኖሩን ካሳየ የጊዜ ገደቡ ቢያልፍም ለምዝገባ የሚያመለክትበትን ጊዜ ኤጀንሲው እስከ 3 ወር ሊያራዝም ይችላል:: በአንቀጽ 66 ድንጋጌዎች መሠረት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በመመስረታቸው ብቻ ሕጋዊ ሰውነት አይኖራቸውም:: የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበራት ከመመዝገባቸው በፊት የሚያሰባስቡት ገንዘብ ወይም ንብረት ከሀምሳ ሺህ ብር በላይ ሊሆን አይችልም:: በሕግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ያልተመዘገበ የተመሰረተ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር እንዲቋረጥ ምክንያት ይሆናል::

አለም አቀፍ ተሞክሮዎችና የበርካታ ዲሞክራሲያዊ አገራት ልምድ እንደሚያሳዩት ማህበራት ሥራቸውን ያከናውኑ ዘንድ እንዲመዘገቡ ወይም ሕጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸው አይገደዱም:: ሕጋዊ ሰውነት ማህበራት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ጠይቀው የሚያገኙት መብት እንጂ በህግ የሚጣልባቸው ግዴታ አይደለም:: የረቂቁ አቋም ግን የዚህ ተገላቢጦሽ ነው:: ህጉ ምዝገባን ግዴታ ያደርጋል:: ሆኖም የሰዎች የመደራጀት መብት በመመዝገብና ባለመመዝገብ ሊወሰን አይገባውም:: በመሆኑም ማህበራት

ባመቻቸው ጊዜ ሁሉ ሕጋዊ ሰውነት እንዲሰጣቸው ሊጠይቁና ያለምዝገባ በተሰማሩበት መስክ መስራት እንደሚችሉ ሊደነገግ ይገባል፡፡

ማህበራት ከመመዝገባቸው በፊት የሚያሰባስቡት የገንዘብ እና ንብረት ጣሪያን በተመለከተም ህጉ እንደዚህ አይነት ገደብ ሊያስቀምጥ አይገባውም፡፡ የሚሰበሰበውን የገንዘብ መጠን አስቀድሞ ለመወሰን የሚቻል ካለመሆኑም በላይ ተገቢነቱም እጅግ አጠያያቂ ነው፡፡ ይህ ገደብ ማህበራትን እንደተመዘገቡ ወዲያው ስራ ከመጀመር ይልቅ ገንዘብ ወደማሰባሰብ እንዲገቡ ያስገድዳቸዋል፡፡

የማህበሩ መቋረጥ የሚኖረው ውጤት ምን እንደሆነ አልተገለጸም፡፡ የማህበር መቋረጥ ምን ማለት ነው ውጤቱስ ምን ይሆናል የሚለው ተዘርዞ ቢቀመጥ የተሻለ ይሆናል ለምሳሌ መስራቾች በራሳቸው ስም ለማህበሩ ጥቅም የገቧቸው ግዴታዎችና ወጪዎች ቢኖሩ ህጋዊ ውጤታቸው ምን እንደሚሆን እንዲሁም ለማህበሩ አላማ የተሰበሰበ ገንዘብ ቢኖር ለማን መሰጠት እንዳለበት በዝርዝር ቢካተት ጥሩ ነው፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

**አንቀጽ 65 አመሰራረት**

1. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት በዚህ አዋጅ የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልተው ሲገኙ እንደተመሰረቱ ይቆጠራል፡፡
2. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማሕበር ህጋዊ ሰውነት እና የሥራ ፍቃድ ሰርተፊኬት ለማግኘት ከፈለገ ለምዝገባ ማመልከት አለበት፡፡

**አንቀጽ 66 የመመሥረት ውጤት**

ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 እንደሚከተለው ቢስተካከሉ

3. የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበራቱ ከመመዝገባቸው በፊት የሚያሰባስቡት ገንዘብ ወይም ንብረት ከብር መቶ ሺ በላይ ከሆነ መሥራቾቹ የተሰበሰበውን ገንዘብ መጠን እና የተደረጉ ወጪዎችን ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለባቸው፡፡ ኤጀንሲው እነዚህን ማህበራት እንዲመዘገቡ ሊያስገድዳቸው ይችላል፡፡
4. ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ባለመመዝገቡ ምሥረታው የተቋረጠ ማህበር በምሥረታው ሂደት ከአባላት መዋጮ ሌላ ያሰባሰበው ገንዘብ ካለ

ተመሳሳይ ዓላማ ላላቸው ወይም ለሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲተላለፍ ኤጀንሲው በፍርድ ቤት ሊያስወስን ይችላል።

**የዘርፍ አስተዳዳሪዎች፡- አንቀጽ 67 እና 68**

በእነዚህ አንቀጾች መሠረት አግባብነት ያሏቸው የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶች በዘርፍ አስተዳዳሪነት በሚኒስቴሩ ይሰየማሉ፣ ፈቃድና ምዝገባን በተመለከተ ለኤጀንሲው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ፣ በማቋቋሚያ ሕጋቸው መሠረት የበ.አ.ድ. እና ማህበራትን የሥራ እንቅስቃሴዎችን ይከታተላሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣ አስፈላጊ እርምጃ ይወስዳሉ። እነዚህ አንቀጾች ተባብሮ ከመስራት ይልቅ ወደ ቁጥጥር የሚያዘነብሉ በመሆናቸው፣ ለዘርፍ አስተዳዳሪዎች ገደብ የለሽ ስልጣን ከመስጠታቸውም በላይ ተደራቢ ተጠያቂነትን ፈጥረዋል። «አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል» የሚለው አገላለጽ ለዘርፍ አስተዳዳሪዎች አላግባብ ሰፊ የሆነ እና ያልተገለጸ ሰፊ እና ለትርጉም ክፍት የሆነ ሥልጣን የሚሰጥ ነው። በእነዚህ አካላት የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች በይግባኝ እንደገና የሚታዩበት ስርዓት በህጉ አልተካተተም።

**የማሻሻያ ሀሳቦች፡-**

እነዚህ አንቀፆች የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ከማህበራት ምስረታ አንስቶ ወደፊትም ስለሚኖራቸው ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ሚና የሚመለከቱ እንደመሆናቸው በረቂቅ አዋጁ የመጀመሪያ ክፍል ቢካተቱ የተሻለ ይሆናል። ስለሆነም የዘርፍ አስተዳዳሪዎች በራሳቸው የቅጣት እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የቴክኒክም ሆነ የአሰራር ጉድለት በበአድና ማህበራት ላይ በሚያገኙበት ጊዜ መወሰድ ስለሚገባው ርምጃ የውሳኔ ሐሳብ ለኤጀንሲው የሚያቀርቡበት እና በኤጀንሲው ውሳኔ መሠረት እርምጃ የሚወደስበት ሁኔታ ቢመቻች የተሻለ ይሆናል፤ ከዚህም በተጨማሪ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች በየራሳቸው የማቋቋሚያ አዋጆች የየራሳቸው ስልጣንና ኃላፊነት ስላላቸው በዚህ ሕግ እንዲሸፈኑ ማድረጉ አስፈላጊ አይደለም።

**ምዝገባና የምዝገባ ጥያቄን አለመቀበል፡- አንቀጽ 69 እና 70**

በአንቀጽ 69 መሠረት ኤጀንሲው ማመልከቻ ሲቀርብለት በአዋጁ የተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አመልካቾቹን በመመዝገብ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ለምዝገባ የሚቀርቡት ሰነዶች የመተዳደሪያ ደንቦችና የማቋቋሚ ሰነዶች እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ኤጀንሲው የሚጠይቃቸው ሌሎች ሰነዶች ናቸው። ለውጭ በአድ ተጨማሪ ሰነዶች ሊቀርቡ ይገባል። በአንቀጽ 70 መሠረት የሚከተሉት የምዝገባ ጥያቄን ውድቅ ሊያደርጉ ይችላሉ፤

- ሊቋቋም የታሰበው የበ.አ.ድ. ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በአዋጁ የተደነገጉትን ተፈላጊ ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ መገኘት፣
- ሊቋቋም የታሰበው በአድ ወይም ማህበር ሕገወጥ ለሆነ የሕዝብን ሰላም ለሚያደፈርስ፣ ወይ የኢትዮጵያን ደህንነትና መረጋገት ለመጉዳት መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል የሚያሰኝ በቂ ምክንያት መኖር፣
- የምዝገባ ማመልከቻው የአዋጁን ወይም በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችን ድንጋቴዎችን የማያሟላ መሆን፣
- በ.አዱ ወይም ማህበሩ የሚመዘገብበት ስም ከሌላ በ.አ.ድ ወይም ማህበር ወይም ከማናቸውም ሌላ ተቋም ስም ጋር የሚመሳሰል መሆን ወይም የሕዝብን ሞራል፣ ወይም ህግን የሚቃረን መሆን
- የበ.አ.ዱ. ወይም ማህበሩ ስያሜ አገር አቀፋዊ ወይም ፌዴራላዊ ሆኖ የአባላት ጥንቅር ወይም የሥራ ቦታው ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና የሌለው መሆን

አለም አቀፍ ተሞክሮዎች እደሚያሳዩት ምዝገባ በአንጻራዊ መልኩ ፈጣን፤ ግልጽና በቀላል ዋጋ የሚፈጸም መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም የምዝገባ ጥያቄን ባለመቀበል የሚሰጥ ውሳኔ በሕግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት ይገባል፡፡ በእነዚህ መመዘኛዎችና በሕገ መንግስቱ እውቅና ከተሰጣቸው የመብት ገደቦች መሰረት በበአድ እና ማህበራት ላይ የተጣሉት ብዛት ያላቸው ገደቦች በጣም ጫናን የሚፈጥሩና አሳማኝ ምክንያቶች ሊቀርቡባቸው የማይችሉ ናቸው፡፡ በዚሁም መሠረት ረቂቁ ለምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ከዘረዘረ በኋላ ኤጀንሲው እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ሰነዶችን ሊጠይቅ ይችላል ብሎ ለመደንገግ ያስፈለገበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ ሃላፊነትን በአግባቡ ላለመወጣት በር ከመክፈቱ በተጨማሪ ሕጋዊ ጠቀሜታ ያለው አይደለም፡፡

የሕዝብን ሰላም ለማደፍረስ፣ ደህንነትና ሰላምን መጉዳት የሕዝብ ሞራል መቃረን የመሳሰሉት ገደቦች አሻሚና አጠቃላይ በመሆናቸው አላግባብ በስልጣን መጠቀምን የሚጋብዙ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ፣ በአዋጅ የተደነገጉትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ያለማሟላት፣ አዋጁን ወይም ደንቦችን አለማሟላት እንደ ነገሩ ሁኔታ ቀላል ወይም ከባድ ሊሆን ስለሚችል በአጠቃላይ ምዝገባን መከልከሉ አሳማኝ ሊሆን አይችልም፡፡ አለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ምዝገባን ለመከልከል የሚቀመጡ መሥፈርቶች ግልጽና ለትረጉም ክፍት ያልሆኑ እንዲሁም ለአስተዳደር መሥሪያቤቶች ደንብ የተተዉ መሆን የለባቸውም፡፡ ሥለዚህ እነዚህ የክልከላ መሰረቶች በህጉ ላይ

በግልጽ መቀመጥ እነዳለባቸው አለም ዓቀፉ የሲቭልና ፖለቲን መብቶች የቃልኪዳን ስምምነት የግድ ይላል፡፡

የሥም ተመሳሳይነት ተቀባይነት ያለው ምክንያት ቢሆንም የአንድ በአድ ወይም ማህበር ስም ከሌላ የተለየ ተቋም ስም ጋር ቢመሳሰል ምዝገባ የሚከለከልበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ ይህ ክልከላ አስፈላጊ የሚሆነው በተመሳሳይ የሥራ ዘርፎች ለተሰማሩ ተቋማት ነው፡፡ በመሆኑም ተመሳሳይ ባልሆኑ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ተቋማት አንድ ዓይነት ስም ቢኖራቸው የማምታታት ችግር ይፈጠራል ተብሎ አይጠበቅም፡፡

ኤጀንሲው በህጉ ላይ በተመለከተው 30 ቀናት ውስጥ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልሰጠ ወይም የማይሰጥ መሆኑን ካላሳወቀ ለቦርዱ ይግባኝ ማለት እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ድንጋጌ ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸውን ሌሎች ተቋማት ለመግዛት ከወጡ ኢትዮጵያውያን ህጎች ለምሳሌ የፕሬስና የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ አንጻር ሲታይ መብትን የሚያጠብ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የምዝገባ ሥርዓት መብትን የመንፈግ አቅም ሥላለው በጥንቃቄ ሊያዝ የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ የበርንታ አገሮች ልምድ ያሳያል፡፡ በፕሬስና የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጆች ላይ መዝጋቢው አካል በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምዝገባውን ካልፈቀደ ወይም የከለከለ መሆኑን ካላሳወቀ አመልካቹ እንደተመዘገበ እንደሚቀጠር ያስቀምጣሉ፡፡ በተመሳሳይ ኤጀንሲው በህጉ ላይ በተመለከተው በ30 ቀናት ውስጥ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካልሰጠ ወይም የማይሰጥ መሆኑን ካላሳወቀ ለቦርዱ ይግባኝ መጠየቅ ሳያስፈልግ አመልካቹ ድርጅት እንደተመዘገበ መቆጠር አለበት፡፡

የአምስት ክልሎች ውክልናን በተመለከተ የተጣለው ገደብ ሕጋዊ መሠረት የሌለውና በህገ መንግስቱ የተረጋገጠውን የመደራጀት መብት የሚፃረር ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በሃሳብ ከሚግባባው ከሌላ ማንኛውም ሰው ጋር የመሰባበሰብና ህጋዊ ለሆነ ዓላማ የመደራጀት መብት አለው፡፡ በማህበር ተደራጅተው ሥራ ሊሰሩ በአቀደበት ክልል ወይም በሌላ የሚያውቁት ወይም ሃሳባቸውን የሚቀበልና አብሮአቸው በማህበር ተደራጅቶ የሚሰራ ሰው ባለማግኘታቸው ብቻ በህገ መንግሥቱ የተረጋገጠላቸው የመደራጀት መብት ሊጣስባቸው አይገባም፡፡

ኤጀንሲው ከተጣሉበት ሃላፊነቶች ውስጥ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት እንዲስፋፉና ተልዕኮዋቸውን በሕግ መሠረት እንዲወጡ ማስቻልና ማበረታታት በመሆኑ

ኤጀንሲው ምዝገባውን ከመከልከሉ በፊት መስራቾቹን አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርጉ ማማከር ይገበዋል፡፡ ክልከላው መሆን ያለበት ይህንን ምክር ለመቀበል ፍቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ብቻ ነው፡፡

የማሻሻያ ሀሳቦች፡-

- ለትርጉም የተጋለጡ አጠቃላይና አሻሚ ቃላት ግልጽ በሆነ መንገድ ሊደነገጉ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በህጉ ላይ በተመለከተው በ30 ቀናት ውስጥ የምዝገባ ሠርተፊኬት ካልሰጠ ወይም የማይሰጥ መሆኑን ካላሳወቀ አመልካቹ ድርጅት እንደተመዘገበ ሊቆጠር ይገባል፡፡
- ለኤጀንሲው ለምዝገባ የሚያስፈልጉ በስም ያልተጠቀሱ ሰነዶችን የመጠየቅ ስልጣን የሚሰጠው ንኡስ አንቀጽ ሊሰረዝ ይገባዋል፡፡
- ደንቦችን ህጎችንና በህግ መሠረት የወጡ ደንቦችን አለማሟላት ምዝገባ የሚያስከለክለው ከባድ ለሆኑ ጉዳዮች ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ምዝገባን የሚያሰከለክሉ ገደቦች ለአስተዳደራዊ ደንቦች መተው ሥለሌለባቸው በአዋጁ ላይ ተጠቃለው ሊመለከቱ ይገባል፡፡
- የሥም ተመሳሳይነት ምዝገባ የሚያስከለክለው ስሙ ከሌሎች በ.አ.ድ ወይም ማህበራት ስም ጋር የተመሳሰለ ከሆነ ብቻ መሆን አለበት፡፡
- በዋናነትም ኤጀንሲው ጥያቄውን ውድቅ የማድረግ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በአድ ወይም ማህበሩ የጎደለውን እንዲያሟላ ሊመክረው እንደሚገባ ግዴታ ሊጣልበት ይገባል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ቅርንጫፍ፡- አንቀጽ 73

አንቀጹ ከደነገጋቸው ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- ማናቸውም በአድ ወይም ማህበር አስቀድሞ ኤጀንሲውን በማሳወቅ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል፡፡
- ለሚከፈተው ቅርንጫፍ የሚሰጠው ስልጣን ራሱን የቻለ የሚያደርገው ወይም በቂ ቁጥጥር እንዳይደረግበት የሚያደርገው ሊሆን አይገባም፡፡
- አንድ በአድ ወይም ማህበር አስቀድሞ ኤጀንሲውን ሳያሳውቅ ቅርንጫፍ ቢያቋቁም እንደ ሕገ ወጥ በአድ ወይም ማህበር ይቆጠራል፡፡ እንዲሁም የወንጀል ኃላፊነትን ያስከትላል፡፡

ለሲቭል ማህበራት ሊረጋገጡላቸው ከሚገቡ መሠረታዊ ነጻነቶች ውስጥ አንዱ የሥራ ቦታቸውን መምረጥ መቻላቸው ነው፡፡ በረቂቅ ህጉ ላይ በአድ እና ማህበራት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት መክፈት ቢፈልጉ በቅድሚያ ለኤጀንሲው ማሳወቅ እንዳለባቸው መመልከቱ ምንም እንኳን የሚያመጣው ችግር ባይኖርም ለምን የሚል ጥያቄ ማስከተሉ ግን አይቀርም፡፡ በተለይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንደሚኖረው በመመሥረቻ ጽሑፉ ላይ ያሰቀመጠ ድርጅት እንደገና ለኤጀንሲው እንዲያሳውቅ ግዴታ መጣሉና የወንጀል ኃላፊነት ማስከተሉ አግባብ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንቀጹ አድራጎቱን ወንጀል ለማድረግ የሚጠቅሰው ድንጋጌ ማለትም አንቀጽ 104 የወንጀል ሃላፊነትን የሚተረጉም ሳይሆን ሥለ ሌላ ጉዳይ (ሥለ ገቢ ማስገኛ) የሚያወራ በመሆኑ የአፃፃፍ ጉድለትም አለበት፡፡

የማሻሻያ ሀሳቦች፡-

- ያለፈቃድ ቅርንጫፍ መክፈት በአስተዳዳራዊ እዕርምጃ፣ ቢቻል በማስጠንቀቂያ የሚታለፍ ጥፋት ቢሆን፡፡
- ሥለ ወንጀል ሃላፊነት የሚደነግገው አንቀጽ 104 ሣይሆን 103 ሥለሆነ አንቀጽ 73/3 በዚሁ ቢታረም፡፡

ፈቃድ ስለማሳደስ፡- አንቀጽ 77

ይህ አንቀጽ ፈቃድ በየሶስት ዓመት መታደስ እንዳለበት ደንግጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፈቃድ ማደስን የተመለከቱ ሌሎች አከራካሪ አንቀጾች ተሰርዘዋል፡፡ ይህ የሚደገፍ ውሳኔ ነው፡፡ ኤጀንሲው ከበአድ እና ማህበራት ሁሉንም ጉዳዮች የተመለከቱ ሪፖርቶችን የመቀበል ስልጣን ስላለው ከዚሁም የተነሳ በአድ ወይም ማህበራቱ በሕጉ መሠረት መስራታቸውን ማረጋገጥ እና ፈቃድ ጭምር ሊሰርዝ የሚችል ከባድ ጥፋት ተፈጽሞ ከሆነ የፍቃድ ማሳደሻ ጊዜው ባይደርስም አስፈላጊውን ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰድ እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ፈቃድ በየ ሶስት አመቱ መሆኑ ተገቢ ነው፡፡ ይህ የተጨመረ ሀሳብ ነው፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የለም

አንቀፅ 78 ፡ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ

በሲቪል ማህበራት አደረጃጀት ላይ ከሚጣሉት ግዴታዎች ውስጥ አንዱ የድርጅቱን ወይም የማህበሩን የገንዘብ እንቅስቃሴ የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታታ ነው። ይህ ግዴታ በሌሎች አገሮች ተመሳሳይ ህጎች ውስጥም የሚገኝ ነው። የድንጋጌው መኖር አጠያያቂ ባይሆንም እእንደዚህ ዓይነት ድንጋጌዎች የሚመሩባቸው መሠረታዊ መርሆች መኖራቸው ግን ሊስተዋል ይገባል። ከዚህ ውስጥም የሂሳብና የድርጅቱን እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ሰነዶች አያያዝ ለሌሎች ድርጅቶች ተፈፃሚ የሚሆኑ የህግ ጥበቃዎች ታሳቢ መሆን አለባቸው። በተለይም የግል ምስጢርን ከመጠበቅ አኳያ የተደነገጉ ህጎችና ህገ-መንግስታዊ ዋስትናዎች ለሲቪል ማህበራትም በእኩልነት ተፈፃሚ ሊሆኑ ይገባል።

የረቂቅ ህጉ አንቀፅ 78 ስለሂሳብ መዝገብ አያያዝ ይደነግጋል። የዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 3 በአድ እና ማህበራት ስሙ ካልተገለፀ ሰው ልገሳ መቀበል እእንደማይችሉና የለጋሾችን ማንነት የሚያሳይ መዝገብ መያዝ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይህንን ድንጋጌ መተላለፍም በቁጥር 103 እእንደተመለከተው በድርጅቱ ላይ ከብር 10,000 ሺህ እስከ ብር 20,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት የሚያስቀጣ ሲሆን በዚህ አድራጎት ተሳትፈዋል የተባሉ ግለሰቦች ደግሞ ከብር 5,000 እስከ ብር 10,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ወይም ከ3 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ እእስራት ሊቀጡ ይችላሉ።

እንደሚታወቀው በተለይም የበአድ ሥራ በበጎ ፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሥራ ነው። ይህ ሥራ የሚከናወነውም ሰዎችን ለመርዳት ቀና ፍላጎት ካላቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች በሚገኝ የገንዘብና የንብረት ልገሳ ነው።እነዚህ ለጋሾች በተለያዩ ምክንያቶች ማንነታቸው እንዲገለፅ ላይፈልጉ ይችላሉ። በተግባርም የሚያጋጥም አሰራር ነው። በረቂቅ ህጉ ላይ በአድና ማህበራት ማንነቱ ካልታወቀ ወገን ልገሳ መቀበል እንደማይችሉ ከመገለፁ በቀር የክልከላው መሠረት አልተገለፀም። የአንድ ድርጅት ህጋዊነት መታየት ያለበት ከሚሰራው ስራ አኳያ እንጂ በገንዘብ ምንጩ መሆን የለበትም። ቁጥጥር መደረግ ያለበት በገንዘቡ አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ሊሆን ይገባል። የለጋሾች ማንነት እንዲገለፅ ማስገደድ የለጋሾችን በህግ የተጠበቀ የግል ምስጢርን እንደመግለፅ ከማስቆጠሩም በላይ በድርጅቶቹ የገቢ ምንጭ ላይ ጉዳት ያደርሳል። ስለዚህ ይህ አንቀፅ

የማሻሻያ ሀሳብ

1. አንቀፁ ቢሰረዝ፤ ይህ ባይቻል እንደሚከተለው ቢስተካከል፤፣
2. በአድ ወይም ማህበራት በተቻለ መጠን የለጋሹን ማንነት በግልፅ የሚያመለክቱ መዝገቦችን መያዝ አለባቸው::

በአድ ወይም ማህበራት ማንነቱ ካልታወቀ ወይም እንዲገለፅ ካልፈለገ ወገን ልገሳ ከተደረገላቸው ሁኔታውን ለኤጀንሲው በማሳወቅ ስጦታውን ድርጅቱ ለተቋቋመበት ዓላማ ብቻ ያውላሉ::

**አንቀፅ 78(5)**

ይህ ድንጋጌ በአድ ወይም ማህበራት የሂሳብ ሰነዶችን ለአምስት ዓመታት ይዘው እንዲቆዩ እና ይህ ጊዜ ከማለቁ በፊት ህልውናቸው የሚያበቃ በአድ ወይም ማህበራት የሥራ መሪዎች ለተወሰነው ጊዜ ሠነዶቹን ጠብቆ የማቆያት ሃላፊነት እንዳለባቸው ያስቀምጣል:: በረቂቅ ህጉ ላይ እንደተመለከተው የሂሳብ ሠነዶችን ለተወሰኑ ጊዜያት ይዞ የማቆየት ሃላፊነት በሌሎች አገሮች ህጎች ላይ እና በአንዳንድ ለጋሽ ድርጅቶች አሰራር ላይ ያለ ነው:: ስለዚህ ረቂቅ ህጉ ይህንን ግዴታ ማስቀመጡ ተገቢ ነው ለማለት ይቻላል::

ይሁን እእንጂ ድንጋጌው ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን ያገናዘበ አይመስልም:: የድርጅቱ ህልውና ካከተመ በኋላ ሠነዶቹ አምስት ዓመት እስኪሞላቸው የድርጅቱ ተቀጣሪ ሠራተኛ የሆነውን «የሥራ መሪ» ሠነዶቹን ይዘህ ቆይ ብሎ ማስገደዱ ከግለሰቡ መብትና ሠነዶችን ይዞ ለማቆየት ከሚጠይቀው ወጪ አንፃር ሊታይ ይገባዋል:: አንድ ሰው በአጋጣሚ በድርጅቱ ህልውና ማብቂያ አካባቢ የሥራ መሪ ሆኖ በመገኘቱ ብቻ የድርጅቱን የሂሳብ ሠነዶች ለአምስት ዓመት ያህል እንዲጠብቅ ማድረጉ የግለሰቡን ሰብዓዊ መብት ይጋፋል::

**የማሻሻያ ሀሳብ**

ንዑስ ቁጥር 5 እንደሚከተለው ቢሰተካከል

5. ኤጀንሲው ሰነዶቹ እንዲወድሙ ወይም በሌላ መንገድ እንዲወገዱ በጽሁፍ ካልፈቀደ በስተቀር ከሂሳብ ሰነድ ጋር በተያያዘ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፬) የተወሰነው የአምስት ዓመት ጊዜ ከማለቁ በፊት የበአዱ ወይም የማህበሩ ህልውና ካከተመ የበአዱ ወይም የማህበሩ የሥራ መሪዎች ሠነዶቹን ለኤጀንሲው ያስረክባሉ::

*ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራ ስለማድረግ፡- አንቀፅ 80*

*የረቂቅ ህጉ አንቀፅ 80 ስለ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት አሰራር ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሂሳብ ሪፖርት በየዓመቱ የሚደረግ ሆኖ ሂሳቡ በተመሰከረለት ኦዲተር ወይም በውስጥ ኦዲተር ወይም ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር መመርመር እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ በመሆኑም ህጉ ሦስት ዓይነት ኦዲተሮችንና የሂሳብ ምርመራ ዘዴዎችን የሚያስብ ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው የአንድ ድርጅት ዓመታዊ በጀቱ ከብር 100,000 በታች በሚሆንበት ጊዜ በውስጥ ኦዲተር ሊመረመር እንደሚችል የሚያስቀምጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጀቱ ከብር 100,000 በላይ በሚሆንበት ጊዜ በውጭ ኦዲተር መመርመር እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡ ሦስተኛው የምርመራ ዓይነት በሁለት መንገዶች የሚከናወን ነው፡፡ በማንኛውም ጊዜ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚደረግ ድንገተኛ ምርመራ አንዱ ዓይነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአዱ ወይም ማህበሩ በህጉ በተመለከተው አምስት ወር ጊዜ ውስጥ የሂሳብ ምርመራ ሳያስደርግ ሲቀር ወይም በውጪ ኦዲተር ማስመርመር የተሸለ ሆኖ ሲገኝ በግዴታ በኤጀንሲው አማካኝነት የሚደረገው ምርመራ ነው፡፡ በግዴታ በኤጀንሲው ትዕዛዝ የሚደረግን የኦዲት ሥራ ወጪ የሚሸፍነው በአዱ ወይም ማህበሩ ወይም ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ የሥራ መሪዎቹ ይሆናሉ፡፡*

*የአንድ ማህበር የገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ ቁጥጥር መደረጉና ማህበሩም በየዓመቱ የኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርብ መጠየቁ የማህበሩን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ አንዱ እና ዋንኛው በመሆኑ የአንቀፁ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይደለም፡፡*

*ይሁን እንጂ እንደዚህ ዓይነት ምርመራዎች ሲደረጉ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው እሣቤዎች በረቂቅ ህጉ ላይ አልተመከቱም፡፡ ድንገተኛ ወይም የግዴታ የሂሳብ ምርመራዎች ሲደረጉ በድርጅቱና ማህበራቱ የአሰራር ነፃነት ላይ አስፈፃሚ አካላት ጣልቃ እየገቡ ሥራቸውን እንዳያውኩ ተገቢ ጥበቃ ሊደረግ ይገባል፡፡ ድንገተኛ ወይም አስገዳጅ የሂሳብ ምርመራዎችን ለማድረግ የግድ የሚሉ ምክንያቶች በግልፅ መታወቅ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ምርመራዎቹ ከመካሄዳቸው በፊት ለማህበራቱ ወይም ድርጅቶቹ በቂ የማስታወቂያ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡*

በአንቀፁ ቁጥር 4 ላይ የተመለከተው «በውጪ ኦዲተር ማስመርመር የተሻለ ሆኖ ሲገኝ» የሚለው ሃረግ ለትርጉም ክፍት የሆነና የድርጅቶቹን ነፃነት የሚፈታተን ነው:: ኤጀንሲው በቁጥር 3 ላይ እንደተመለከተው በማንኛውም ጊዜ ድንገተኛ ኦዲት ማስደረግ እየቻለ እንደገና በቁጥር 4 ላይ በድርጅቱ ወጪ የሚካሄድ የግዴታ ኦዲት እንዲደረግ መደረጉ ተገቢነት የለውም::

የማሻሻያ ሀሳብ

- 80(3). የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ ቢኖርም ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አንድ በአድ ወይም ማህበር ተቀባይነት ባለው የሂሳብ አሰራር መሠረት እየተመራ ሥላለመሆኑ በቂ ማስረጃ ካለው ኤጀንሲው በማንኛውም ጊዜ በቂ ማስታወቂያ በመስጠት የበአዱ ወይም የማህበሩ ሂሳብ በውስጥ፣ በውጪ ወይም ኤጀንሲው በሚሾመው ኦዲተር እንዲመረመር ሊያደርግ ይችላል::
- 80(4). የበአዱ ወይም ማህበሩ ሂሳብ የሂሳብ ዓመቱ ባለቀ በአምስት ወራት ውስጥ ካልተመረመረ እና ለዚህም የሥራ መሪዎቹ በቂ ምክንያት ማቅረብ ካልቻሉ ኤጀንሲው ኦዲተር ሾሞ ማስመርመር ይችላል::
- 80(5). በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት በኤጀንሲው በተሾመው ኦዲተር ለተከናወኑ ማንኛውም የኦዲት ሥራዎች ወጪ የሚከፍለው የሚመለከተው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ይሆናል:: ሆኖም ሂሳቡ ያልተሰራው በሥራ መሪዎቹ ጥፋት ነው ብሎ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ካመነ በፍትሐ ብሔር ህጉ መሠረት ወጪውን ኃላፊነቱ ከሚመለከታቸው የሥራ መሪዎች ሊጠይቅ ይችላል::

የማሻሻያ ሀሳብ

አንቀፅ 86፡- ሠነዶች እንዲያቀርቡ የማዘዝና ሪከርዶች እንዲመረመሩ የማድረግ ሥልጣን ይህ አንቀፅ ከአንቀፅ 85 ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ የዚህን አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የአንቀፅ 85 ንዑስ አንቀፅ 4 በማድረግ ሌላውን በመሰረዝ ድግግሞሹ እንዲቀር ቢደረግ::

አንቀፅ 87: ስብሰባዎችን ስለማስታወቅ

ይህ አንቀፅ ማህበራት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎችን ጊዜና ቦታ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው እንዲያሳውቁ ይደነግጋል:: የዚህ ፅሁፍ አዘጋጆች የበርካታ አገራትን ሲቪል ማህበራት ህጎችን ተመልክተዋል:: በተመለከቷቸው አገራት ውስጥም ሆነ

ተቀባይነት ባላቸው አለም አቀፍ ደረጃዎች እንደዚህ ዓይነት ድንጋጌ የለም:: ሠዎች ህጋዊ ለሆነ ዓላማ አንድ ጊዜ ከተደራጁ በኋላ የሚያደርጓቸውን ስብሰባዎች የማሳወቅ ግዴታ ሊጣልባቸው አይገባም:: በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት ላይ እንደተቀመጠው ሃሳብን የመግለፅ፣ የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶች የቅድመ ምርመራ ሥራ የሚፈፀምባቸው ሊሆኑ አይገባም:: ማህበራት አባላቶቻቸውን ለበርካታ ጊዜያት ሊሰበስቡ ይችላሉ:: አባላቶቻቸውን ከሰባት የሥራ ቀናት ባነሰ ጊዜ ውስጥም ለመጥራት ሊገደዱ ይችላሉ:: በዚህ ድንጋጌ መሠረት ግን ይህንን ለማድረግ አይፈቀድላቸውም:: ስብሰባን የማስታወቁ ህጋዊ ዓላማም ምን እንደሆነ አይታወቅም::

**የማሻሻያ ሀሳብ**

1. አንቀፁ ሙሉ በሙሉ ቢሰረዝ፣ ወይም
2. “ማንኛውም ማህበር የማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያደርገውን ስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ቅጂ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው መላክ አለበት” በሚል ቢስተካከል

**አንቀፅ 89: መረጃ ስለመግለፅ**

ይህ አንቀፅ በአንቀፅ 85 እና 86 ላይ እንደተመለከተው የሚናገረው መረጃን ስለመግለፅ ነው:: መረጃን አስመልክቶ በአንቀፅ 85 ላይ በሰፊው የተገለፀ በመሆኑ የዚህ አንቀፅ አስፈላጊነት አጠያያቂ ነው::

**የማሻሻየሳ ሃሳብ**

1. አንቀፁ ድግግሞሽን ለማስቀረት ቢሰረዝ፣ ወይም
2. የአንቀፅ 85 ንዑስ አንቀፅ ሆኖ ቢካተት፤

**አንቀፅ 90: አስተዳደራዊና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪዎች**

ይህ አንቀፅ በአድና ማህበራት ከገቢያቸው ውስጥ ምን ያህሉን ለአስተዳደርና ለዓላማ ማስፈፀሚያ ማዋል እንዳለባቸው ይደነግጋል:: በዚህም መሠረት በአድ ወይም ማህበራት በየበጀት ዓመቱ ከሚያወጡት ውጪ ከ70 በመቶ የሚያንሰውን ለድርጅቱ ዓላማ ማስፈፀሚያና ከ30 በመቶ የማይበልጠውን ደግሞ ለድርጅቱ አስተዳደራዊ ወጪ ማዋል

እንዳለባቸው እንዲሁም ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን ለዓላማው ማስፈፀሚያ የሚያውል በአድ ወይም ማህበር በመንግስት የተለያዩ ማበረታቻዎች ሊደረጉለት እንደሚችል አንቀፁ ይገልፃል፡፡ይህንን ድንጋጌ ተላልፎ መገኘትም በቁጥር 103 ሥር በተመለከተው መሠረት በገንዘብ ወይም በእስራት ያስቀጣል፡፡

የአንዳንድ አገራት ህጎች እንዲህ ዓይነቱን የቁጥጥር ሥርዓት ይዘው እናገኛለን፡፡ ይሁን እንጂ የእነዚህ አገራት ልምድ እንደሚያሳየው ወደ ተግባር በሚኬድበት ጊዜ ችግር ማጋጠሙ አልቀረም፡፡ ለዚህ ችግር ዋንኛው መንስዔ ህጉ የድርጅቶቹን ተለዋዋጭ የሥራ ባህርይ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለመቻሉ ነው፡፡ ለአንዳንድ ድርጅቶች 30% የአስተዳደር ወጪ ትልቅ ሊመስል ይችላል፡፡ በተለይም ብዙ ሥራዎች ከዋና መስሪያ ቤታቸው ውጪ ላላቸው ድርጅቶች፡፡ በአንፃሩ ሥራቸው በጥናትና ምርምር ላይ የሆኑና አብዛኛው ሥራቸው በዋናው መስሪያ ቤት የሆኑ እንዲሁም አዲስ የሚመሰረቱ ድርጅቶች አስተዳደራዊ ወጪያቸው ከፍ ማለቱ አይቀርም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አንቀፁ በአባላት መዋጮ ብቻ ስለሚሰሩ ድርጅቶችም ተፈፃሚ እንዲሆን የተዘጋጀ ይመስላል፡፡ አንዳንድ ማህበራት ለአባላቶቻቸው ጥቅም በአባላቶቻቸው መዋጮ ብቻ ወይም ከፍተኛውን ገቢ ከዚህ የሚያገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ማህበራት በዚህ ድንጋጌ ለመግዛት ማሰብ የሰዎችን በገንዘባቸው የፈለጉትን የመወሰን መብታቸውን ይነካል፡፡ ይህ ድንጋጌ ቷላሚ ማድረግ ያለበት በህዝብ ስም ከለጋሽ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ወይም መንግስት የተሰበሰበን ገቢ እንጂ ከአባላት የተሰበሰንና በአባላት ተቀባይነት ያለውን ወጪም ጭምር ሊሆን አይገባም፡፡

የአስተዳደራዊ ወጪን ( ምንነት አስመልክቶ በህጉ ላይ የተሰጠው ትርጉም ክበባዊ (circular) ትርጉም በመሆኑ ሃሳቡን መረዳት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ህጉ በአንቀፅ 2(14) ላይ አስተዳደራዊ ወጪን ለመተርጎም የሞከረ ቢሆንም «አስተዳደራዊ ሥራ» የሚባሉትን ባለመተርጎሙ አንቀፁን ለመረዳት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ይህንን አስመልክቶ በትርጉም ክፍል ላይ የተብራራ ሥለሆነ ተጨማሪ ማብራሪያ አያስፈልግም፡፡

አስተዳደራዊና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪዎች የሚለው ሀሳብ ክበባዊ እና አደናጋሪ በመሆኑ ለቀጥታ እና ቀጥተኛ ላልሆኑ ወጭዎች የሚወጡ ወጭዎች በሚል መልኩ ቢቀመጥ የተሻለ ገላጭ ይሆናል፡፡ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጭዎች ትርጉም በትርጉም ክፍሉ ላይ ለማብራራት ተሞክሯል ፡፡በመሆኑም ከዚህ በኋላ አስተዳደራዊና የዓላማ ማስፈፀሚያ ወጪዎች የሚለውን ሀሳብ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጭዎች በሚል ይገለጻል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ**

የአንቀፁ ተፈፃሚነት ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ብቻ ቢሆን፤ የአንቀፁ ተፈፃሚነት ለማህበራትም ጭምር መሆን አለበት ከተባለ ለአባላቶቻቸው ጥቅም እና ለሦስተኛ ወገኖች ጥቅም በሚሰሩት መካከል እንዲሁም የገቢ ምንጫቸው ከአባላት በሆነና የገቢ ምንጫቸው ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ወይም መንግስት በሆኑት መካከል ልዩነት ቢደረግ፡፡ በዚህም መሰረት አንቀፁ እንደሚከተለው ቢስተካከል፤

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ልገሳውን ካደረጉለት ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ያደረገው ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከተቀበለው ገንዘብ ውስጥ <u>ቀጥተኛ ለሆኑ ወጪዎች</u> ከ70% የማያንሰውን እንዲሁም ለሌሎች <u>ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች</u> ከ30% የማይበልጠውን ማዋል አለበት፡
2. ከላይ በንዑስ ቁጥር አንድ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆነ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ከሥራው ጠባይ የተነሳ ወይም በሌላ ምክንያት ከገቢው ከ30% በላይ ለ <u>ቀጥተኛ ላልሆኑ ወጪዎች</u> የሚያደርግ ከሆነ ሁኔታውን ለኤጀንሲው በማሳወቅ ኤጀንሲው እስከ 40% ከፍ እንዲያደርግ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡
3. ለጋሽ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የበጎ አድራጎት ድርጅቱን አቅም ለማጠናከር የሚሰጡት ልገሳና ለዚህ ሥራ ድርጅቱ የሚያወጣው ወጪ እንደ <u>ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች</u> አይታሰብም፡፡

**አንቀፅ 92. የንብረት ጥበቃ**

ይህ ድንጋጌ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበርን ንብረት ጥበቃ አስመልክቶ የተደነገገ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ላይ የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ንብረት በተገቢው ሁኔታ የተጠበቀ አይደለም ብሎ ሲያምን ኤጀንሲው ሊወስዳቸው ስለሚችላቸው እርምጃዎች ተመልክቷል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ንብረትን አስመለክቶ ኤጀንሲው ቁጥጥር እንዲያደርግ መደረጉ ተገቢና በሌሎች አገሮችም ያለ አሰራር ነው፡፡ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችም የሚያሳዩት ይህንን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ድንጋጌ አስመልክቶ የሚነሱ ሁለት አበይት ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም አንደኛው ኤጀንሲው በቁጥር አንድ ላይ የተመለከቱትን እርምጃዎች ከመውሰዱ በፊት ለድርጅቶቹ ወይም ማህበራቱ የበላይ ጠባቂ አካላት ሁኔታውን በቅድሚያ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ኤጀንሲው እርምጃውን መውሰድ ያለበት የድርጅቱና የበላይ ኃላፊዎቹ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ለመፈፀም ፍቃደኛ ካልሆኑ ብቻ መሆን አለበት፡፡

ሁለተኛው ነጥብ በቁጥር 2 ላይ የተመለከቱትን እርምጃዎች ይመለከታል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በኤጀንሲው የተሰጠውን ትዕዛዝ እስኪፈፅም ከድርጅቱ ወይም ከማህበሩ ጋር ውሎች እንዳይደረጉ፣ ክፍያዎች፣ እንዳይፈፅሙ፣ የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ንብረቶችና ዕዳዎች እንዳይመለሱ ሊያግድ እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ ይህ ድንጋጌ የድርጅቱን ወይም የማህበሩን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል የኤጀንሲውንም ሥልጣን ከሚገባው በላይ ያሰፋና እሱ ከሣሽና ዳኛ እንዲሆን የሚያደርገው ነው፡፡ የድርጅቱ ዕዳ እንዳይከፈል፣ ንብረት እንዳይመለስ፣ ድርጅቱ ገንዘብ እንዳይሰጠውና ውል እንዳይፈፀም ማድረግ ድርጅቱን ከማፍረስ የሚተናነስ አድራጎት አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ይህ ድንጋጌ በበአድና በአባላት መዋጮ ለአባላት ጥቅም በሚሰሩ ድርጅቶች መካከል ልዩነት ማድረግ አለበት፡፡ አንቀፁ ተፈፃሚ መሆን ያለበት ለህዝብ ወይም ለሦስተኛ ወገን ጥቅም እንሰራለን ብለው ከህዝብ፤ ከድርጅቶች ወይም ከመንግስት ገንዘብ በተቀበሉ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ እንጂ ለአበላቶቻቸው ጥቅምና በአባላቶቻቸው መዋጮ ለሚሰሩ ማህበራት ጭምር መሆን የለበትም፡፡ መንግስትም እራሱ ያልሰጠውን ወይም በዜጎቹ ስም ያልተገኘውን ሃብት ለማስተዳደር መሞከር የለበትም፡፡

ምክረ ሃሳብ

1. አንቀፁ በማህበራት ላይ ተፈፃሚ ሳይሆን በፊደል «ለ» ላይ የተመለከተው ፊደል «ሀ» ቢሆን፤

2. የአሰራር ሥርዓቱን እንዲያሻሽል ፍቃደኛ ባልሆነው የሥራ መሪ ላይ ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ ሥልጣን ላለው የድርጅቱ አካል ያሳውቃል።

3. በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሥልጣን ያለው አካል ተገቢ እርምጃ የማይወስድ ከሆነ ኤጀንሲው የድርጅቱ የሥራ መሪዎች እእንዲታገዱ ለቦርዱ አቤቱታ ያቀርባል። ቦርዱ የኤጀንሲውን አቤቱታና የድርጅቱን መልስ መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል።

አንቀፅ 93: የሥራ መሪዎችን ስለማንሳትና መተካት
ይህ ድንጋጌ በአንቀፅ 71 ላይ የተመለከቱትን የገደብ መስፈርቶች በመተላለፍ የሥራ መሪ የሆኑ ሠዎች ከኃላፊነታቸው የሚነሱበትን ሁኔታ ይደነግጋል። አንቀፅ 71 ላይ የተቀመጡት ገደቦች፤

1. በማጭበርበር ወይም ታማኝነትን በማጓደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣ፤

2. በማናቸውም ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሲቪል መብቱን የተገፈፈና መብቶቹ ያልተመለሱለት ከሆነ፤

3. በሕግ መሠረት ከችሎታ ማጣት የተነሳ መሥራት የማይችል ከሆነ፤

4. በፍርድ ክልከላ የተደረገበት ከሆነ፤

5. ኢትዮጵያ ውስጥ ከሌለና አለመኖሩ ለበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማሕበሩ ትክክለኛ አስተዳዳር እንቅፋት የሚሆን ከሆነ ናቸው።

በሥራ መሪነት የሚቀመጡ ሠዎች ብቃትና ታማኝነት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀመጡ ድንጋጌዎች ተገቢነት ያላቸው ናቸው። አንቀፅ 71 እና 93 መታየት ያለባቸው በዚህ መንፈስ ነው። ይሁን እንጂ ለኤጀንሲው በተሰጠው ሥልጣን ላይ ተገቢ ትኩረት ሊደረግ ይገባል። የኤጀንሲው ሥልጣን በተቻለ መጠን ቁጥጥርና ምርመራ ማድረግ እንጂ በተጨማሪነት ውሣኔ ሰጪ መሆን የለበትም። ሥልጣኑም የኤጀንሲው ሳይሆን የኤጀንሲው ዳይሬክተር መሆን አለበት። የኤጀንሲው ዳይሬክተር እንደዚህ ዓይነት ሠዎች በሥራ መሪነት መቀመጣቸውን ካረጋገጠ ሥልጣን ያለው የማህበሩ

አካል ተቢውን ማስተካከያ እንዲያደርግ ማዘዝና ይህ ካልተፈፀመ ግን ቦርዱ ውሣኔ እንዲሰጥለት መጠየቅ ይችላል።

የማሻሻያ ሀሳብ

1. ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የማህበር መሪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፩ ከተመለከቱት መመዘኛዎች አንዱን ያጓደለእንደሆነ ሥልጣን ባለው የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ አካል እንዲነሳና በሌላ እንዲተካ ኤጀንሲው ለቦርዱ ያመለክታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የሥራ መሪ በሌላ እስኪተካ ወይም ቦርዱ ውሣኔ እእስኪሰጥ ድረስ ከኃላፊነት እንዲታገድ የኤጀንሲው ዳይሬክተር ሊያዝ ይችላል።

3. ቦርዱ በሰጠው ውሣኔ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ወይም የሥራ መሪው ቅሬታታካላቸው ቅሬታቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ ።

አንቀፅ 94: ፍቃድን ስለማገድና መሰረዝ

ይህ ድንጋጌ የአንድ በአድ ወይም ማህበር የሥራ ፍቃድ በኤጀንሲው ስለሚታገድበትና ስለሚሰረዝበት ምክንያቶች ይደነግጋል። ፍቀድን ማገድና መሰረዝ ከድርጅቱ ህልውና ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው። እንደዚህ ዓይነት በህልውና ላይ የሚሰጡ ውሣኔዎች ደግሞ በፍ/ቤት መሆን አለባቸው። ይህ ባይቻል እንኳን በተሰጠው ውሣኔ ላይ በፍ/ቤት ይግባኝ መጠየቅ እንደሚቻል ለዚህም በቂ ጊዜ ሊሰጠው እንደሚገባ የተለያዩ አገራት ልምዶች ያሳያሉ። ለዕገዳውና ለስረዛው የሚያበቁት ምክንያቶችም ሊታረሙ የማይችሉ ከባድ ግድፈቶች መሆን አለባቸው። በዘህ ረገድ የደቡብ አፍሪካ ልምድ በአስተዳደር መስሪያ ቤትና በማህበራት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በዕርቅ መፈታት እንዳለባቸው ያሳያል።

የማሻሻያ ሀሳብ

1. ዕገዳውን ወይም ስረዛውን የመወሰን ሥልጣኑ የፍርድ ቤት ወይም የቦርድ ቢሆን፤

2. በንዑስ ቁጥር 2 የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸውን የመወሰን ሥልጣኑ የኤጀንሲው ሳይሆን የቦርዱ ቢሆን፤

3. ቦርዱ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ቅሬታ ካለው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል:: በሚል ቢሰተካከል::

**አንቀፅ 98: አነስተኛ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት**

ይህ ድንጋጌ ስለአነስተኛ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚደነግግ ሲሆን አንድን ድርጅት አነስተኛ የሚያስብሉትን መስፈረርቶች አስቀምጧል:: በዚህም መሠረት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ በመጨረሻ የሂሳብ ዓመቱ ጠቅላላ ገቢው ከ50,000 ብር በላይ ካልሆነና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ካልሆነ እንደ አነስተኛ የበጎ አድራጎት ድርጅት ይቆጠራል:: ይህንንም ተከትሎ የድርጅቱ የበላይ አካል የንብረት ማስተላለፍና ክፍፍል፤ የአላማዎችና የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥ ማድረግ እንደሚችል ተቀምጧል። በእርግጥ እነዚህ ውሣኔዎች የሚሰጡት በአደራ ጠባቂ ወይም በቦርድ አባላት 2/3ኛ ድምፅ ሲሆን ውሣኔዎቹም በኤጀንሲው መፅደቅ አለባቸው::

ይህ ድንጋጌ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው በርካታ ጉዳዮችን ይዟል:: በቅድሚያ በርዕሱና በአካሉ (the title and the body ) መካከል ልዩነት አለ:: «ማህበራት» በርዕሱ ላይ የተመለከቱ ሲሆን በአንቀፁ አካል ውስጥ ግን የሉም:: አካሉ የሚያወራው ስለ በአድ ብቻ ነው:: ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ውሣኔ የሚሰጡት የአመራር አካላት የድርጅቱ «አደራ ጠባቂዎች» ወይም «ቦርድ» ተብሎ መጠቀሱን ስናይ ይህ አንቀፅ ተፈፃሚነት ያለው ለሁለት ዓይነት ድርጅቶች ብቸ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል:: ምክንያቱም በህጉ ላይ እንደዚህ ዓይነት የአመራር አካላት ያላቸው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትና የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ብቻ ናቸው:: እንዲሁም በንኡስ ቁጥር 1 ላይ "የድርጅቱ የበላይ አካል የሚከተሉትን ሊፈጽም ይችላል" ከተባለ በኂላ እንደገና በንኡስ ቁጥር 2 ላይ ውሳኔው በድርጅቱ «አደራ ጠባቂዎች» ወይም «ቦርድ» 2/3ኛ ድምጽ ብቻ ነው መባሉ አንቀጹ እርስ በርሱ እንዲጋጭ ያደርገዋል። የጠቅላላ ጉባኤ ባለው ድርጅት ወይም ማህበር ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ጉባኤው እንጂ ቦርድ አይደለም። ህጉ በጠቅላላ ጉባዔ የበላይነት ስለሚተዳደሩ የበጎ አድራጎት ማህበራት ወይም ማህበራት የሚለው ነገር የለም::

ሦስተኛውና ዋናው አከራካሪ የሚሆነው እንዴት አንድን ድርጅት በአንድ ዓመታዊ የሒሳብ ገቢው ብቻ አነስተኛ ነው ብሎ መወሰን ይቻላል? የሚለው ነው፡፡ የአንድ ድርጅት የአንድ ዓመት ጠቅላላ ገቢው ከ50,000 ብር ሳይበልጥ ዓመታዊ ወጪው በሚሊየኖች የሚቆጠር ሊሆን የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡ ዘንድሮ ምንም ገቢ ሳይኖረው አቻምና ባስገባው ገቢ ብቻ ለሁለትና ከዚያም በላይ ለዓመታት የሚሰራ ድርጅት ዘንድሮ ገቢው ከ50,000 ብር በማነሱ አነስተኛ ድርጅት ሊባል አይችልም፡፡

ሌላው ከዚህ አንቀጽ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነጥብ የተቀመጠው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ አሁን አገራችን ከደረሰችበት የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ አንፃር ይህ የገንዘብ ጣሪያ በጣም አነስተኛ በመሆኑ መጠኑ ከፍ ሊል ይገባል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

1. ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢና ወጪ ከ100,000.00 ብር በላይ ካልሆነና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ካልሆነ በስተቀር የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የበላይ አካል የሚከተሉትን ሊፈጽም ይችላል፤

   ሀ. የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ሁሉም ንብረቶች ለሌላ የበጐ አድራጐት ድርጅት እንዲተላለፍ ወይም እንዲከፋፈል፤

   ለ. የመተዳደሪያ ደንቡ ሁሉንም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ዓላማዎች በጐ አድራጐት ወደሆኑ ሌሎች አላማዎች በመለወጥ እንዲሻሻል ማድረግ፤

   ሐ. የስራ መሪዎች የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን በማስተዳደር ረገድ ሊከተሏቸው የሚገቡ ስነሥርዓቶችን በተመለከተ የበጐ አድራጐት ድርጅቱን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ማድረግ፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማንኛውም ውሣኔ የሚተላለፈው በድርጅቱ ወይም በማህበሩ የበላይ አካል አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ብቻ ነው፤

3. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚከናወኑ ተግባራት ተፈጻሚነት የሚኖራቸው በኤጀንሲው ሲጸድቁ ብቻ ነው፤

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ኤጄንሲው የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹ ወይም ማህበራቱ በንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ)-(ሐ) የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንዲፈጽሙ ውሳኔ መስጠት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 103:- ቅጣት**

ይህ ድንጋጌ በወንጀል ህጉ እና በረቂቅ ህጉ መሠረት ሊያስቀጡ የሚችሉ የጥፋት አይነቶችና ቅጣቶችን ይዟል፡፡ እንደ ማንኛውም ሌሎች አዋጆች ረቂቅ ህጉን መተላለፍ ሊያስቃጣ እንደሚችል በቁጥር 1 ላይ የተመለከተ ሲሆን በቁጥር 2 ላይ ግን በአዋጁ አንቀጽ 78፣79፣84፣ እና 90 ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚተላለፍ ድርጅት ወይም ማህበር ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ) እስከ ብር 20,000.00 (ሃያ ሺህ) የገንዘብ ቅጣት እና ተደጋጋሚ አጥፊ ከሆነ ደግሞ የመፍረስ ውሣኔ እንዲሁም አጥፊው ግለሰብ ሆኖ ከተገኘ ከብር 5,000.00 (አምስት ሺህ) እስከ 10,000.000 (አስር ሺህ) ብር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ወይም ከ3 እስከ 5 ዓመት የሚደርስ እሥራት ሊቀጣ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

በአንቀጽ 78፣ 79፣ 84፣ እና 90 የተቀመጡት ግዴታዎች የሂሣብ መዝገብ የመያዝ፣ ሥሙ ካልታወቀ ለጋሽ ሥጦታ የመቀበል፣ የሂሣብ መግለጫ ለኤጀንሲው መላክ፣ የባንክ ሂሣብ ለኤጀንሲው ማሣወቅ እና ከጠቅላላ ገቢ ላይ ከ 70% የማያንሰውን ለአላማ ማስፈፀሚያ እና ከ 30% የማይበልጠውን ለአስተዳደራዊ ወጪዎች ማሥፈፀሚያ ማዋል ናቸው፡፡ እነዚህን ግዴታዎች ያለመተግበር ከላይ የተመለከተውን ቅጣት በድርጅቱ ወይም በማህበሩ እና በሥራ መሪዎቹ ላይ ያስከትላል፡፡

በአንቀጽ 103 (1) ላይ የተመለከተው ቅጣት አይነት ማህበራት ወይም በአድ እንደ ማንኛ ውም ሰው ህጉን በመተላለፋቸው የሚጣል በመሆኑ ተፈፃሚነቱ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ ሆኖም ድርጅቶች ወይም ማህበራቱ እና የሥራ መሪዎቹ ለተደጋግሚ ቅጣት እንዳይዳረጉ ተገቢ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ በአንቀጽ 78 እና 79 ላይ እንደተመለከተው በወቅቱ የሂሣብ ሪፖርት ያለማቅረብ የሚያስከትለው ውጤት በአንቀጽ 80 ላይ ተመልክቷል፡፡ በአንቀጽ 80 መሠረት አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር በወቅቱ ሂሣቡን አስመርምሮ ለኤጀንሲው ካላሳወቀ ኤጀንሲው ኦዲተር በመሾም ሂሣቡ እንዲሠራ እንደሚያደርግ እና ወጪውንም ከድርጅቱ ወይም ከሥራ መሪዎቹ ሊጠይቅ

እንደሚችል ተመልክቷል። በመሆኑም እንደገና የበጐ አድራጐት ድርጅቶቹ ወይም ማህበሩ በአንቀጽ 103 (2) ሥር በተጨማሪ በወንጀል እንዲቀጣ መደረጉ በተለይም ከቅጣቱ ከባድነት አንፃር ሊታይ የሚገባው ነው።

የኤጀንሲውን ትዕዛዝ ወይም የአዋጁን ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎች የማያከብር እንዲሁም በወቅቱ ተፈላጊ ሪፖርት የማያቀርብ በጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ፍቃዱ ሊታገድና ሊሠረዝ እንደሚችል በአንቀጽ 94 ላይ በግልጽ ተመልክቷል። ከዚህ ቅጣት በተጨማሪ በአንቀጽ 103 (3) ላይ እንደገና ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እና የሥራ መሪዎቹ እንዲቀጡ መደረጉ ቅጣቱን ተደራራቢና አስፈሪ ያደርገዋል።

*የማሻሻያ ሀሳብ*

*አንቀጽ 103 (2) እና (3) ቢወጡ እና በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ መሰረት ብቻ እንዲተዳደሩ ቢደረግ*

*አንቀጽ 104 የገቢ ማሥገኛ ሥራዎች*

*ይህ አንቀጽ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ መሠማራት የሚችሉበትን ቅድመ ሁነታ ያስቀምጣል። በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ለመሰማራት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፡-*

- ከኤጀንሲው የጽሁፍ ፍቃድ ማግኘት፣
- ገቢው ለማህበሩ ወይም ለድርጅቱ አባላት ወይም ተጠቃሚዎች የማይውል መሆን አለበት፣
- ገቢው ለዓላማ ማስፈፀሚያ ብቻ የሚውል መሆን አለበት፣
- የገቢ ማመንጨቱ ሥራ ከድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓላማ ጋር የሚሄድ መሆን አለበት፣
- ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ለገቢ ማስገኘቱ ሥራ የተለየ የሂሣብ መዝገብ መያዝ አለበት
- በተጨማሪም ትርፍ ለማግኘት በሚሠሩ ሥራዎች ላይ ሌሎች ህጐች ያላቸው ተፈፃሚነት እንደተጠበቀ ነው።

የሲቪል ማህበራት ህጎች ከሚወጡባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የማህበራቱን ገቢ በማስገኘት ሥራ ላይ የመሰማራት መብት ለማስጠበቅም ጭምር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ረቂቅ ህጉ በአድ እና ማህበራት ገቢ በሚያሥገኝ ሥራ ላይ እንዲሠማሩ መፍቀዱ የሚበረታታእአርምጃ ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት በልገሣ ላይ ጥገኛ ሣይሆኑ እራሣቸውን ችለው እንዲንቀሣቀሱ በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሠማሩ መደረጉ ለሥራቸው ቀጣይነት እና ነፃነት በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም ከውጭ አገር የሚመጣን የገንዘብ ጥገኝነት እቀንሳለሁ ወይም ሙሉ በሙሉ አስቀራለሁ ብሎ ለተነሣ ህግ ድርጅቶችና ማህበራቱ በአገር ውስጥ ገቢ የሚያገኙበትን መንገድ ማስፋትና ማበረታታት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የአንቀጽ 104ን አፈፃፀምን ስንመለከት ሊመለሱ የሚገባቸው በርካታ ጥይቄዎች መኖራቸውን እናስተውላለን፡፡ በቅድሚያ አንቀጹ ድርጅቶችና ማህበራት በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ከመፍቀድ ውጭ ያስቀመጠው አንዳችም የተለየ ጥበቃ የለም፡፡ ይልቁንም ለቁጥጥር የቆመና በአድ ወይም ማህበራት በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ የሚሰማሩበትን እድል አጥብቦ ያስቀመጠ ነው፡፡ የሌሎች አገራት ልምድ እንደሚያሳየው ከገቢ ማስገኛ ሥራዎች ጋር የሚደነገጉ አንቀጾች የተለዩ ጥበቃዎችን አብረው ያሰፍራሉ፡፡ ህጉ የተለየ ጥበቃ የማይሰጥ ከሆነ ጠቀሜታው አጠያያቂ ነው፡፡ ድርጅቶችና ማህበራት ተመዝግበው ህጋዊ ሰውነት ካገኙ ንብረት የማፍራትና በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ መሰማራት ህገ መንግስታዊ መብታቸው ነው፡፡ ረቂቅ ህጉ ይህንን ህገ መንግስታዊ መብት መልሶ ከማስተጋባት በላይ መብቱ የሚተገበርበትን የተለየ ጥበቃ ሊያደረግ ይገባዋል፡፡

ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ለመሰማራት በቅድመ ሁኔታነት ከተቀመጡት ጉዳዮች አንዱ የኤጀንሲውን ፍቃድ በቅድሚያ ማግኘት ነው፡፡ የዚህ ቅድመ ሁኔታ አስፈላጊነት እጅግ አጠያያቂ ነው፡፡ የኤጀንሲውን ቅድሚያ ፍቃድ ማግኘት የሚያስፈልገው ለምንድ ነው? ማህበራት ወይም በጎ አድራጎት ድርጅቶች ህጋዊ ሰውነት ያላቸውና ለህጋዊ ዓላማ የተቋቋሙ እስከሆነ ድረስ በፈለጉትና ለሥራቸው ገቢ ሊያስገኝላቸው በሚችል ሥራ የመሰማራት መብታቸውን ለመጠቀም ለምን ፍቃድ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ ድርጅቶች ፍቃድ የሚያገኙትና የሚተዳደሩት እንደማንኛውም የንግድ ተቋም መሆኑን ህጉ እራሱ

እየተናገረ ለምን ከኤጀንሲው ፍቃድ ማግኘት እንደሚያስፈልጋቸው ግልጽ አይደለም። ይልቁንም ኤጀንሲው የድርጅቶቹንና የማህበራቱን በፈለጉት ህጋዊ ሥራ ላይ የመሠማራት መብትን እንዲጥስ በር ይከፍታል። በተጨማሪም ድርጅቶቹን ለተደራራቢ ቢሮክራስያዊ አሠራር ይዳርጋቸዋል። በህጉ የሚገኝ የተለየ ጥቅምና ጥበቃ ሳይኖር የኤጀንሲውን ፍቃድ ማግኘት አስፈላጊ መሆኑ ጠቃሚ አይደለም።

የኤጀንሲው ዋንኛ ኃላፊነት መሆን ያለበት ድርጅቶች በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ተሠማርተው ያገኙትን ገንዘብ ለድርጅቱ ዓላማ ማዋል ያለማዋላቸውን መቆጣጠር ነው። ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የሚያገኙትን ገንዘብ ድርጅቶቹ በቅድሚያ ለኤጀንሲው የማሳወቅና ፍቃድ የማግኘት ግዴታ እንደሌለባቸው ሁሉ በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ ለመሠማራት የኤጀንሲውን ፍቃድ ማግኘት ሊጠበቅባቸው አይገባም።

የድርጅቶቹ ወይም ማህበራቱ ገቢ ለአባላቶቻቸው እንዳይከፋፈል ጥበቃ መደረጉ ተገቢ ነው። ድርጅቶችን ወይም ማህበራቱን ከንግድ ድርጅቶች ከሚለዩዋቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ ይህ ነው። በመሆኑም ከገቢ ማስገኛ ሥራዎች የተገኘውን ገንዘብ የድርድቶቹ አባላት እንዳይከፋፈሉት ጥበቃ ማድረጉ ተገቢ እና በሌሎች አገሮችም ህግ ውስጥ ያለ አሠራር ነው። ይሁን እንጂ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው አንድ ነጥብ ቢኖር በረቂቅ ህጉ ላይ እንደተመለከተው ከገቢ ማስገኛ ሥራው የተገኘው ትርፍ "ለተጠቃሚዎች" ሊተላለፍ የማይችል መሆኑ ነው። አንድ ድርጅት ወይም ማህበር የሦስተኛ ወገኖችን ወይም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የገንዘብ አቅም ለመገንባት በማሰብ ሊቋቋም ይችላል። ይህንን ዓላማውን ለማሳካት በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ተሠማርቶ ያገኘውን ገንዘብ ለእነዚህ ተጠቃሚዎች ቢሠጥ የሚያስከትለው ህጋዊ ችግር የለም። አደጋ የሚኖረው ትርፉ ለድርጅት ወይም ማህበራቱ አባላት ከተከፋፈለ ወይም ድርጅቱ ወይመም ማህበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ ውጭ እንዲውል ከተደረገ ነው። ለተጠቃሚዎች ትርፍ እንዳይከፋፈል የሚከለክል ህግ ያላቸው አገራትም ለማግኘት አስቸጋሪ ነው።

ሦስተኛው መስፈርት የገቢ ማስገኛ ሥራው ከድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ሊኖረው ይገባል የሚለው ነው። ይህ ገደብ መካተቱ ለምን እንዳስፈለገ ግልጽ አይደለም። ድርጅቶቹ ወይም ማህበራቱ በህጋዊ ስራ ላይ እስከተሰማሩ ድረስ እና

በህጉ የተለየ የጥቅም ጥበቃ እስካልተሠጣቸው ድረስ በፈለጉትና በሚያዋጣቸው የሥራ መስክ ሊሠማሩ ይገባል፡፡ አሁንም በድጋሚ ልናስተውል የሚገባው ከገቢ ማስገኛ ሥራ ጋር በተያያዘ የሚጣሉ ገደቦች በዋነኛነት ማተኮር ያለባቸው ከሥራው የተገኘው ትርፍ ለድርጅቱ ወይም ማህበሩ ዓላማ ማስፈፀሚያ መዋሉን መቆጣጠር እንጂ የሥራውን ዓይነት ወይም ባህሪይ መሆን የለበትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከውጪ በሚገኝ ገንዘብ ላይ ከፍተኛ ማዕቀብ የጣለ ህግ እንደገና በአገር ወስጥ ሊገኝ የሚችልን የገቢ ምንጭ አገር በቀል ድርጅቶችና ማህበራት እንዳያገኙ የተለያዩ አሣሪ ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጡ እነዚህ ድርጅቶች እንዳያድጉና እንዳይስፋፉ ማድረግ የለበትም፡፡

በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ከመሰማራት ጋር ተያይዞ ሌላው የሚታየው ነጥብ  ከላይ እንደተገለፀው ህጉ የሚሠጠው የተለየ ጥበቃ ነው፡፡ በረቂቅ ህጉ ላይ የተለየ ጥበቃ ሊኖር እንደማይችል በቁጥር 4 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የተለያዩ አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው ግን በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ የተሰማሩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት ከገቢ ወይም ትርፍ ግብር ወይም ከሁለቱም ነፃ ይደረጋሉ፡፡ በመሆኑም ረቂቅ ህጉ እንደነዚህ አይነት ጥቅማጥቅም ሆነ ምዝገባና ፍቃድ ለማግኘት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ የማያደርገው ድጋፍ ሣይኖር ወደ ስራው ለመግባት የኤጀንሲውን ፈቃድ ማግኘት እንዲሁም ስራው ከድርጅቱ ዓላማ ጋር የተያያዘ መሆን እንዳለበት ማስቀመጡ ፍትሃዊ አይደለም፡፡

**የማሻሻያ ሃሳብ**

አንቀጽ 104 እንደሚከተለው ቢስተካከል

1. የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ለበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበር አባላት ሊከፋፈል የማይችል እና ገቢው ለዓላማው ማስፈፀሚያ የሚውል የገቢ ማመንጨት ስራዎችን ሊያከናውን ይችላል፡፡
2. ገቢ የሚያስገኙ ስራዎችን የሚሰራ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎቹን በተመለከተ የተለዩ የሂሣብ መዛግብት መያዝ አለበት

3. የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ትርፉን ለአባላቱ አከፋፍሎ ወይም የተለየ የሂሣብ መዛግብት ሳይይዝ ቢገኝ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 94 መሰረት  አግባብነት ያለውን እርምጃ ይወስዳል

4. በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ የተሠማሩ የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ ስለሚያገኙት የገቢ እና ትርፍ ግብር አከፋፈል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያወጣል::

<u>አንቀጽ 105 አቤቱ እና ይግባኝ</u>

ይህ ድንጋጌ ኤጀንሲው አቤቱታዎችን በ15 ቀናት ውስጥ ማስተናገድ እንዳለበት፣ ኤጀንሲው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል እንዲሁም በቦርዱ ውሣኔ ቅሬታ ያለው ኢትዮጵያዊ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ኢትዮጵያዊ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከኢትዮጵያ የስነ ስርዐት ህግ ጋር በተጣጣመ መልኩ በሁለት ወር (በ60) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል::

ለሚቀርቡ አቤቱታዎች መልስ የሚሰጥበት ጊዜ መወሠኑ እና ለተሰጠው ውሣኔ የአስተዳደር እና የፍርድ ቤት ይግባኝ ሥርዓት መዘርጋቱ ጠቃሚ ነው:: እንደሚታወቀው ህጉ ለኤጀንሲው በአንድ ድርጅት ህልውና ላይ መወሰንን ጨምሮ በርካታ ሥልጣኖችን ሠጥቶታል:: በመሆኑም ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ እንዲቀርብ መደረጉ ተገቢ አሠራር ነው:: ይሁን እንጂ ይህ አንቀጽ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችንም በውስጡ አካቶ ይገኛል::

በመጀመሪያ እና በዋናነት የሚታየው የአንቀጹ አድሎአዊነት ነው:: አንቀጹ የይግባኝ መብትን የሚፈቅደው ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሰው፤ በአድ ወይም ማህበር ብቻ ነው:: እንደሚታወቀው የኢፌዲሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 31 የመደራጀት መብትን "ለማንኛ ውም ሰው" በዜጋ እና በውጭ አገር ሰዎች መካከል ልዩነት ሣያደርግ አረጋግጧል:: በተጨማሪም ኢትዮጵያ የፈረመችውና የአገሪቱ የህግ አካል የሆነው አለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት እና ሌሎችም ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው አለም አቀፍ የሠብአዊ መብት ሰነዶች እንዲህ አይነት ልዩነቶች እንዳይደረግ ይደነግጋሉ:: ስለዚህ፤ የረቂቁ አንቀጽ 105 (3) በፍርድ ቤት ይግባኝ የመጠየቅ መብትን ለኢትዮጵያውያን ብቻ መገደቡ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 31 እና ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሠነዶች አንፃር ታይቶ ሊሻሻል ይገባዋል::

ህገ መንገሥቱ በአንቀጽ 37 ላይ ፍትህ የማግኘት መብትን ሲያስቀምጥ በተመሳሳይ በዜጐችና በውጭ አገር ሰዎች መካከል ልዩነት አላደረገም፡፡ ፍትህ የማግኘት መብት የተረጋገጠው "ለማንኛውም ሰው" ሥለመሆኑ በህገ መንግሥቱ ላይ በግልጽ የተቀመጠ እውነታ ነው፡፡ ስለዚህ የውጭ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ድርጅታቸውን እንደ ውጭ ድርጅት አድርገው የሚያስመዘግቡ ኢትዮጵያዊያን እና የወጭ አገር ድርጅቶች በፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ሥልጣን በተሠጠው አካል ኤጀንሲውና ቦርዱ በሰጡት አስተዳደረዊ ውሣኔ ላይ ቅሬታቸውን እንዳያቀርቡ መከልከሉ ህገመንግሥታዊ አይደለም፡፡

ሁለተኛው አሣሣቢ ጉዳይ ይግባኝ የሚባልበት ነጥብ የህግ ብቻ እንዲሆን መወሰኑ ነው፡፡ በህጉ ላይ የተቀመጡትና ብዙውን ውሣኔ የሚፈልጉት ጉዳዮች ከህግ ይልቅ የፍሬ ነገር መሆናቸው እየታወቀ የይግባኝ መብትን ለህግ ጥያቄ ብቻ እንዲሆን መደረጉ ፍትህ የማግኘት መብትን ያጣብባል፡፡ በፍሬ ነገር ጉዳይ ላይ ብቻ ይግባኝ ለፍ/ቤት የማቅረብ ልምድ በእርግጥም በአገራችን የህግ ሥርዓት ውስጥ ያለ ነው፡፡ ለምሳሌ በታክስ ገዳይ እና በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ይህ አሠራር የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን በእነዚህ ተቋሞች ውስጥ የመጀመሪያውን ውሣኔ የሚሰጡት አካላት የዳኝት መሰል /guasi Judicial/ ሥልጣን የተሠጣቸውና አሠራራቸውም በተቻለ መጠን በፍ/ቤት ሥርዓት የሚመራ ነው፡፡ በረቂቅ ህጉ ላይ ያሉት ውሣኔ ሰጪ አካላት ማለትም ኤጀንሲውና ቦርድ ግን አስተዳደራዊ እእንጂ የዳኝነት / Judicial/ ሥልጣን የላቸውም፡፡

ሦስተኛው ከይግባኝ መብት ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ ይግባኝ ለማለት የተሰጡት ጊዜያት ናቸው፡፡ ለቦርዱም ይሁን ለፍ/ቤት ይግባኝ ለመጠየቅ የተሠጠው የ15 ቀናት ግዜ በጣም አጭር ነው፡፡ በፍ/ቤት ባሉ መደበኛ ጉዳዮች የይግባኝ ጊዜ 60 ቀናት መሆኑ እእየታወቀ በረቂቅ ህጉ ላይ ይህ ጊዜ እንዲያጥር የተፈለገበት ህጋዊ ምክንያት ገልጽ አይደለም፡፡ አለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንዲሚያሳዩት በአድ እና ማህበራት በተወሰነባቸው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለመጠየቅ በቂ ጊዜ ሊሠጣቸው ይገባል፡፡

**የማሻሻያ ሃሣብ**

አንቀጽ 105 እንደሚከተለው ቢስተካከል

1. ኤጀንሲው (ዳይሬክተር) ማንኛውንም በአሰራሩ ላይ የሚቀርብለትን አቤቱታ ተቀብሎ በ ፲፭ ቀን ውስጥ መወሰን አለበት
2. ኤጀንሲው (ዳይሬክተር) በሰጠው ማንኛውም ውሣኔ ላይ ቅሬታታያለው ሰው ውሳኔው በተሰጠ በአንድ ወር ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል:: ቦርዱ የቀረበለትን ይግባኝ በ15 ቀናት ውስጥ መርምሮ መወሰን አለበት:: ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳዳራዊ ውሣኔ ይሆናል::
3. ማናቸውም ቦርዱ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬ□ ያለው ሰው ውሣኔው በተሠጠ በአንድ ወር ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀርባል::
4. በዚህ አንቀጽ መሰረት በይግባኝ ሂደት ላይ የሚገኝ የምዝገባ ወይም የስረዛ ጉዳይ ከሆነ የሚመለከተው አካል የመጨረሻ ውሳኔእስከሚሰጥእንዳልተመዘገበ ወይም እንዳልተሰረዘ ይቆጠራል

<u>አንቀጽ 111:- የመሸጋጋሪያ ድንጋጌዎች</u>

ይህ አንቀጽ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ስለተገኙ መብቶችና ግደታዎች መቀጠል እንዲሁም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተመዘገቡ በአድ እና ማህበራት አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ገዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ እንዳለባቸው ይደነግጋል::

ይህን ድንጋጌ አስመልክቶ ያለው አሳሳቢ ጉዳይ በንዑስ ቁጥር 2 የተመለከተው የአንድ ዓመት ጊዜ ነው:: ቀድሞ የተመዘገቡ ድርጅቶችና ማህበራት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደገና በአዲሱ ህግ መሠረት መመዝገብ እንዳለባቸው አንቀጹ ቢገልጽም በዘህ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ድርጅቶቹና ማህበራቱ አስቀድመው በቀድሞው ህግ መሠረት የጀመሯቸው ሥራዎች መቀጠልና ማጠናቀቅ እንዳለባቸው የሚለው ነገር የለም:: ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጋር በተደረገው የመጀመሪያ ዙር ውይይት ድርጅቶቹ ሥራቸውን በአዲሱ ህግ መሠረትም ባይሆን ለአንድ አመት ሊቀጥሉ እንደሚችል አብራርተዋል:: ይሁን እንጂ አሁን በቀረበው ረቂቅ ህግ ላይ ያለው አንቀጽ ይህንን መንፈስ የያዘ አይደለም::

አስቀድሞ የነበረ አንድ ድርጅት ወይም ማህበር እራሱን በአዲሱ ህግ መሠረት ለመለወጥና ለማደራጀት ሰፊ ጊዜ ያስፈልገዋል:: የጀመሯቸውን ሥራዎች በገቡት የኘ ሮጀክት ውል መሠረት አጠናቀው ለመንግሥትና ለተጠቃሚዎች ማስረከብ አለባቸው:: ከዚህ ቀደም የነበሩ ኘሮገራሞች የተሠሩት አስቀድሞ የነበረውን የህግ ማዕቀፍ መሠረት

አድርገው ሲሆን የአንድ ኘሮጀክት የዕድሜ ዘመን ከሦስት እስከ አምስት ዓመት ሊወስድ እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ድርጅቶቹንና ማህበራቱን የጀመራችሁትን ሥራ አቋርጣችሁ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በአዲስ ህግ መሠረት ተመዝገቡ ማለት ድርጅቶቹንና ማህበራቱን ብቻ ሣይሆን መንግሥትን፣ ተጠቃሚውን ህብረተሰብ እና ዕርዳታውን ያደረጉትን ወገኖች ሁሉ የሚጐዳ ይሆናል፡፡

ሌላው ሊታሰብበት የሚገባው እራሱን ገና ከህጉ መውጣት በኂላ ማደራጀት የሚጀምረው የኤጀንሲው እና የዘርፍ አስተዳዳሪዎች አቅም ነው፡፡ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸውን አሁን ያሉትን ማህበራትና በአድ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ረቂቅ ህጉ በሚያዘው መስፈርት መሠረት መዝግቦ ማስተዳደር ይቻላል ወይ የሚለው አጠያያቂ ነው፡፡ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ እንኳን ብንሄድ አንድ ማህበር ያቀረበውን ኘሮጀክት መርምሮ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚወስደውን ጊዜ ቀላል አይደለም፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ቀድሞ በነበረው ሕግ የተገኘ መብትና ግዴታ ይህን አዋጅ እስካልተቃረነ ድረስ ይቀጥላል፡፡
2. ቀደም ሲል የተመዘገቡ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው፡፡